በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የኦዳ ቡልቱም ዩኒቨርሲቲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የኦዳ ቡልቱም ዩኒቨርሲቲ የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡ ኦዲታችን ፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል::

የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ዩኒቨርሲቲው ያቀረባቸው የሂሳብ መግለጫዎች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው:: ኦዲቱ

የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የኦዳ ቡልቱም ዩኒቨርሲቲ የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣

የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ፣

1. ከመመሪያ ውጭ በሳጥን መቀመጥ ካለበት በላይ የሰኔ 30/2009 ሂሳብ ሪፖርት ብር 256,073.78 በሳጥን የሚገኝ ጥሬ ገንዘብ ተቀምጦ መገኘቱ፣
2. በዩኒቨርሲቲው "ቢ" ሂሳብ ቁጥር 10001711044158 ውስጥ ብር 7,481,706.59 ፈሰስ ሳይደረግ የሚገኝ መሆኑን ተረጋግጧል::
3. ለመደበኛ የተፈቀደው በጀት በሰኔ 30 ሚዛኑ ዜሮ መሆን ሲገባው፣ የሰኔ 30/2009 ሂሳብ ሪፖርት በባንክ ያለ ገንዘብ ብር **1,932,793.46** የሚታይ ቢሆንም፣ የባንክ ስቴትመንት ላይ ምንም ገንዘብ የማይታይና ዜሮ ሚዛን ሲሆን፣ ሪፖርቱ እና ባንክ ስቴትመንቱ የማይጣጣም መሆኑን ተረጋግጧል::

የገቢ ሂሳብ፣

4. በድምሩ ብር 5,083,210.00 ለዩኒቨርሲቲው በገቢ ደረሰኝ ገቢ የተደረገው ገቢም ሆነ ወጪው በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (TR) ተመዝግቦ ሪፖርት ያልተደረገ በመሆኑ ገቢ የሆነው ገንዘብ በትክክል ለታለመለት ዓላማ ስለመዋሉ ለማረጋገጥ አልተቻለም::

5. ዩኒቨርሲቲው በተከታታይ የትምህርት ፕሮግራም ከሚያስተምራቸው ተማሪዎች የሰበሰበውን በድምሩ ብር 638,123.00 የገቢ ሂሳብ ገቢም ሆነ ወጪው ተመዝግቦ ሪፖርት ያልተደረገ እና ስለወጪውም የሚገልጽ ምንም ማስረጃ የሌለው መሆኑን ተረጋግጧል፡፡
6. በማጠቃለያ ደረሰኝ መሂ/64 ተጠቃሎ መመዝገብ ሲገባው ህጋዊነትና በሌለው ወረቀት በማሳተም በማጠቃለል በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (TR) ብር 652,674.49 የተመዘገበ መሆኑና በውስጥ ገቢ መመዝገብ ሲገባው፣ በፋይናንስ ምንጭ በመደበኛ በጀት ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
7. ዩኒቨርሲቲው በሀገር ውስጥ ለሚማሩ መምህራን መመሪያው በሚፈቅደው መሰረት ከሐምሌ 2008 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30/2009 ዓ.ም ከተከፈላቸው ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም በአጠቃላይ ብር 48,686.00 የስራ ግብር ያልተቀነሰ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡
8. የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር **221,439.16** እና ከተከፋይ ሂሳብ ተቀናሽ ብር **17,719.32** በድምሩ ብር **239,158.48** ከተከፈለው ክፍያ ላይ መቀነስ ሲገባው ተቀንሶ ለግብር ሰብሳቢው መ/ቤት ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ገቢ ያልተደረገ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

<u>የወጪ ሂሳብ፣</u>

9. ብር 2,808,873.09 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ተመዝግቦ ወጪ የሆነ ገንዘብ በሂሳብ እንቅስቃሰ መዝገብ (TR) ያልተመዘገበ እና በሪፖርት ያልተካተተ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡
10. ብር **451,489.15** በወጪ መመዝገብ ሲገባው፣ ባልተለመደ የሂሳብ ምዝገባ በተከፋይ ሂሳብ በመንግስት መ/ቤቶች መካከል ሌሎች ተከፋይ ሂሳቦች ተመላሽ በ5028 ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡
11. በድምሩ ብር 476,221.57 የሚመለከተው አካል ሳይፈቅድ ከደንብና መመሪያ ውጭ የተከፈለ ሲሆን የተከፈላቸው ሰራተኞች ስለመስራታቸው የሚገልጽ የሰዓት መቆጣጣሪያ ቅጽ ከወጪ ሰነዱ ጋር ባለመቅረቡ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
12. ከነኢማ ሁሴን የመኪና ጌጣጌጥ ችርቻሮ ንግድ የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች ግዥ በመፈጸም ብር 57,960.00 የተከፈለው አሸናፊው ድርጅት ያቀረበው የዋጋ ማቅረቢያ ሰነድ ተሰርዞ እና ተደልዞ ግዥ የተፈጸመ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡
13. በድምሩ ብር 229,990.00 መመሪያን መሰረት ያላደረገ የክፍያ ተመን ሳይኖር ያለአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡
14. በድምሩ ብር 345,899.99 ከደንብና ከመሪያ ውጭ በቀጥታ ግዥ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

15.በድምሩ ብር 4,875,722.48 አንድ ላይ አሰባስቦ ግዥን መፈጸም ሲገባው በመከፋፈል በዋጋ ማቅረብያ ግዥ የተፈጸመ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

16.ከመመሪያ ውጭ ለተማሪዎች ህብረት ተወካይና ለሰላም ፎረም አባላት በሚል በየወሩ ለሞባይል ካርድ ግዥ በመፈጸም በድምሩ ብር 37,400.00 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

17.የሰዓት መቆጣጣሪያ ሳይፈርሙና ስራ ላይ ስለመሆናቸው ማስረጃ ሣይኖር ብር 108,729.99 ደመወዝ ተከፍሎ መገኘቱን ተረጋግጧል፡፡

18.በድምሩ ብር 293,921.20 መከፈል ከነበረበት በላይ በልዩነት ውሎ አበል ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

19.በድምሬ ብር 1,811,879.63 የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ቀርቦ ሂሳቡ መወራረድ ሲገባው በዱቤ የሽያጭ ደረሰኝ ሂሳቡ ተወራርዶ የተገኘ መሆኑን ተረጋግጧል ፡፡

<u>ተሰብሳቢ ሂሳብ፣</u>

20.በድምሩ ብር 2,584,146.70 የተሰብሳቢ ሂሳብ በወቅቱ ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡

<u>የተከፋይ ሂሳብ፣</u>

21. በድምሩ ብር 2,270,377.77 ተከፋይ ሂሳቦች ለባለመብቱ ሳይከፈሉ ተገኝቷል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 21 በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ መግለጫዎች ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም. የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

<u>ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፣</u>

ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊደረግባቸው፤ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

- በሂሳብ ማመዛዘኛ ሪፖርት የሚታየው የባንክ ሂሳብ እና የባንክ ቋት ሚዛን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በየወሩ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ በየውሩ ተዘጋጅቶ የማይመዛዘን መሆኑን ተረጋግጧል፡፡
- በሳጥን የሚገኘው ጥሬ ገንዘብ በየጊዜው ተቆጥሮ በሂሳብ ክፍል ከሚያዘው የጥሬ ገንዘብ ቋት ጋር መመዛዘን ቢገባውም ተቆጥሮ የማይመዛዘን መሆኑን በኦዲቱ ለማረጋገጥ ችለናል፡፡

- በድምሩ ብር 27815706.14 ስራ ላይ ያልዋለ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

ሌሎች ጉዳዮች፣

ንብረት፣

- የንብረት አያያዝ፣ አመዘጋገብ እና አስተዳደር የውስጥ የቁጥጥር ሥርአቱ ደካማ ለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ልዩ ልዩ፣

- በኮምፑዩተር ሳይንስ ትምህርት መስክ የተደረገው የቅጥር ሁኔታ ፍትሐዊነት የለሌው፣ ግልጸኝነት የጎደለ፣ አዋጅን መሠረት ያላደረገ፣ ተጠያቅነትን የሚያስከትልና አግባብነት የለሌው ስራ መሆኑን በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኦዳ ቡልቱም ዩኒቨርሲቲ
የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

መግቢያ፣

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የኦዳ ቡልቱም ዩኒቨርሲቲ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዩኒቨርሲቲውን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓላማ፣

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት፣

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት ያደረገው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው ፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ /የኦዲት አስተያየት/ ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች ፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል፡፡

አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል ፡፡

ይሁን እንጂ ኦዲቱ በኦዳ ቡልቱም ዩኒቨርሲቲ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሳብ መግለጫዎቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ሲሆን የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል።

1. **የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ፣**

1.1.1 ግኝት፣ በካዚና ውስጥ እንዲቀመጥ ከተፈቀደው መጠን በላይ መገኘቱ፣

የፌዴራል መንግስት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 ዓ.ም አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውና ለጥቃቅን ወጪዎች መሸፈኛ የተፈቀደው ገንዘብ መጠን አሁን ካለው የገንዘብ የመግዛት አቅምና በተለይም ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እያስፈጸሙ ካሉት ከፍተኛ የኢንቨስትመንት ስራ አንጻር ለጥቃቅን ወጪዎች የተፈቀደው የገንዝብ መጠን ዝቅተኛ በመሆኑ፣ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በካዝና እንዲይዙ የሚፈቀድላቸው የጥቃቅን ወጪዎች መሸፈኛ የገንዘብ መጠን ከብር 100,000.00 ያልበለጠ ይሆናል በሚል እንዲሻሻል እንዲደረግ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በቀን 30/07/2007 በተጻፈው ደብዳቤ አሳውቋል። ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲውን የ2009 በጀት ዓመት የፋይናንስ አፈፃፀም ስርዓት ስለትክክለኛነቱ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በሳጥን ከብር 100,000.00 በላይ መያዝ እንደለሌበት ቢታወቅም ከመመሪያ ውጭ በሳጥን ያለ ገንዘብ /cash on Hand 4101/ መቀመጥ ካለበት በላይ የሰኔ 30/2009 ሂሳብ ሪፖርት ላይ ብር 256,073.78 በሳጥን የሚገኝ ጥሬ ገንዘብ ቢታይም የጥሬ ገንዘብ የቆጠራ ማስረጃ የለሌ መሆኑን ተረጋግጧል።

1.1.2 ስጋት፣

የመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት ያለደረገ አሰራር አለመከተል ተጠያቅነትን ከማስከተሉ በተጨማሪ የመንግስት ውስን ሀብት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል።

1.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

በሂሳብ ሪፖርት በሳጥን የታየው የገንዘብ መጠን ተጣርቶ ወደ ባንክ ገቢ መደረግ አለበት። ለወደፊትም እንደዚህ አይነት ስህተት እንዳይከሰት ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን በላይ በሳጥን እንዳይያዝ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል።

1.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

በካዝና ውስጥ የተገኘው በወቅቱ ሳይወራረድ በተሰበሰበ ሂሣብ የነበረ እናበጥሬ ገንዘብ ስላልሆነ ለወደፊት በቦታው ላይ ተጨማሪ የሰው ኃይል ቅጥር በማከናወን ክትትልና ቁጥጥራችንን በማጠናከር በተሰጠን አቅጣጫ መሰረት የምንሰራ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

1.2.1 ግኝት፣ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራና የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ የማይዘጋጅ ስለመሆኑ፣

የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ-8 ንዑስ አንቀጽ 8 በፍደል መ/ በሂሳብ ማመዛዘኛ ሪፖርት ላይ የሚታየው የባንክ ሂሳብ እና የባንክ ሌጀር ሚዛን ትክክለኛነት በየወሩ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ በማዘጋጀት መረጋገጥ እንዳለበት መመሪያው ያዛል፡፡ በተጨማሪም በአንቀፅ 10 ንዑስ አንቀጽ 2 ከሚቀርበው ሪፖርት ጋር ከባንክ ስቴትመንት በዓመቱ መጨረሻ ድህረ ሂሳብ ማመዛዘኛ ሪፖርት እና የመ/ቤቱ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ሠርተፊኬት ተያይዞ መቅረብ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው፤

- በሂሳብ ማመዛዘኛ ሪፖርት የሚታየው የባንክ ሂሳብ እና የባንክ ቋት ሚዛን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በየወሩ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ ማዘጋጀ ቢኖርበትም በየውሩ ተዘጋጅቶ የማይመዛዘን መሆኑን ተረጋግጧል፡፡
- በሳጥን የሚገኘው ጥሬ ገንዘብ በየጊዜው ተቆጥሮ በሂሳብ ክፍል ከሚያዘው የጥሬ ገንዘብ ቋት ጋር መመዛዘን ቢገባውም ተቆጥሮ የማይመዛዘን መሆኑን በኦዲቱ ለማረጋገጥ ችለናል፡፡

1.2.2 ስጋት፣

በሳጥን የሚገኘውን የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ በማድረግ በሂሳብ ክፍል ከሚገኘው የጥሬ ገንዘብ ሌጀር ጋር የማይታረቅ ከሆነ መመሪያ ከመጣሱም በተጨማሪ የመንግሥት ገንዘብ ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

በየወሩ መጨረሻ ከባንክ የሚሰጠው የባንክ ሂሳብ እንቅስቃሴ መግለጫ ዩኒቨርሲቲው ከሚይዘው የባንክ ሂሳብ ሌጀር ጋር በየወሩ እየተገናዘበ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ (Bank Reconciliation) የማይዘጋጅ ከሆነ በባንክ ያለው ገንዘብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሊያስቸግር ይችል ይሆናል፡፡

1.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

የፋይናንስ ክፍሉ በየጊዜው የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ እያደረገ የጥሬ ገንዘብ ማመዛዘኛ መሥራት ይጠበቅበታል፡፡ በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ተዘጋጅቶ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሚቀርበው የሂሳብ ሪፖርት በጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ሠርተፊኬት የተደገፈ ሊሆን

ይገባል፡፡ የሥራ ክፍሉ የባንክ ሂሳብ እና የባንክ ሌጀር ሚዛን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በየወሩ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ ማዘጋጀት አለበት፡፡

1.2.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ተቋሙ አዲስ ከመሆኑ አንጻር ያለብንን የሰው ኃይል እጥረትና የክፍሎች ክፍተትን በመቅጠርና በተከታታይ ስልጠና በመስጠት የታየውን ችግር የምንቀርፍ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

1.3.1.<u>ግኝት</u>፣ <u>ፈሰስ ያልተደረገ ሂሳብ፣</u>

የፌዴራል መንግስት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 ክፍል ስድስት አንቀጽ-34 ንዑስ አንቀጽ 2/በመንግስት ስም የተሰበሰበ ማናቸውም ዓይነት የቀጥታ ገቢ ሂሳብ ወይም ከልዩ ልዩ አገልግሎት የሚሰበሰብ ገቢ በሕግ በተለየ ሁኔታ እንዲሰራበት የተፈቀደ ካልሆነ በስተቀር በበጀት ዓመቱ ውስጥ በየጊዜው ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት የባንክ ሂሳብ ፈሰስ መደረግ ይኖርበታል ይላል፡፡ በዚህ መሰረት ዩኒቨርሲቲው ከተለያዩ የገቢ ምንጮች የሰበሰበውን ገንዘብ በመመሪያው መሰረት ስለመተግበሩ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ2009 በጀት ዓመት የሰበሰበው ገቢ ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት የባንክ ሂሳብ ፈሰስ ማድረግ ሲገባው፣ በዩኒቨርሲቲው "ቢ" ሂሳብ ቁጥር 10001711044158 ውስጥ ብር 7,481,706.59 ፈሰስ ሳይደረግ የሚገኝ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

1.3.2 <u>ስጋት፣</u>

በመመሪያው መሰረት የተሰበሰበው ገቢ ወደ መንግስት ካዜና ፈሰስ ካልተደረገ የመንግስት የበጀት አሸፈፈን ስርዓትን ከመጉዳቱም በተጨማሪ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

1.3.3 <u>የማሻሻያ ሀሰብ፣</u>

ማንኛውም የተሰበሰበ ገቢ በልዩ ሁኔታ ተቋሙ እንዲጠቀምበት ከተፈቀደው እና በመደበኛ በጀት እንዲጠቀሙ ከተፈቀደው በስተቀር ተራፊ በጀት በመመሪያው መሰረት ወደ መንግስት ፈሰስ መደረግ አለበት፡፡

1.3.4.<u> የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

- ከኦሮሚያ ግብርና ቢሮ ትምህርታቸውን ለማሻሻል የተከፈለ ፈንድ መሆኑና ለዚሁ ለሚሰጠው አገልግሎት ተከፋይ ብር መሆኑ፣

- መምህራን ከተለያዩ ለጋሽ ድርጅቶች ለጥናትና ምርምር የተላከና የሚከፈል መሆኑ
- ከዚሁ ውጭ ሆኖ ፈሰስ ያልተደረገውን በመለየት በህጉ መሰረት የማስተካከያ እርምጃ የምንወስድ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

1.4.1.<u>ግኝት፤ የባንክ ሂሳብ በሚመለከት፣</u>

የፌዴራል መንግስት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 ዓ.ም አንቀጽ 37 ንዑስ አንቀጽ 1 ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት ፈሰስ የሚደረገውን ሂሳብ ተከታትሎ የማስፈጸም እና የሚፈለግበትን የፈሰስ ሂሳብ መዝግቦ በመያዝ የፈሰስ ሂሳብ ገቢ ተደርጎ መጠናቀቁን ለሚኒስቴሩ ከሀምሌ 30 በፊት ሪፖርት የማድረግ ኃላፊነት እንዳለበት ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲውን የ2009 በጀት ዓመት የፋይናንስ አፈፃፀም ስርዓት ስለትክክለኛነቱ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ለመደበኛ የተፈቀደው በጀት በሰኔ 30 ላይ ሚዛኑ ዜሮ መሆን ሲገባው የሰኔ 30/2009 ሂሳብ ሪፖርት በባንክ ያለ ገንዘብ /cash at Bank 4103/ ብር **1,932,793.46** የሚታይ ቢሆንም፣ በሰኔ 30/2099 የባንክ ስቴትመንት ላይ ምንም ገንዘብ የማይታይና ዜሮ ሚዛን ሲሆን፣ ሪፖርቱ እና ባንክ ስቴትመንቱ የማይጣጣም መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

1.4.2. <u>ስጋት</u>፣

በባንክ የለሌ ገንዘብ እንዳለ ተደርጎ ሪፖርት ማድረግ ተቋሙ የቁጥጥር ስርዓት እንደለሌው ከማሳያቱም በተጨማሪ የሂሳብ ሪፖርቱን ተዓማንነት ሊያሳጣ ይችላል፡፡

1.4.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ዩኒቨርሲቲው የውስጥ የቁጥትር ስርዓትን በመዘርጋት በባንክ ያለውና በቋት ያለ ገንዘብ ማመዛዘን አለበት፡፡ ስለዚህ በባንክ የለሌው ገንዘብ እንዳለ ተደርጎ ሪፖርት የተደረገው ተጣርቶ የማስተካከያ እርምት ሊወሰድ ይገባል፡፡ ለወደፊትም እንደዚህ አይነት ስህተት እንዳፈጠር ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

1.4.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ከባንክ ወጪ ሆኖ ሌጀር ላይ ያልተቀናነሰ እና የምዝገባ ስህተት ስለሆነ ለቀጣይ በጀት ዓመት ስህተቶች እንዳይደገሙ እንሰራለን፡፡

2. የገቢ ሂሳብ

2.1.1.ግኝት፣ ተመዝግቦ ሪፖርት ያልተደረገ የውስጥ ገቢ ሂሳብ፣

የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ-8 የሂሳብ አያያዝ ዝርዝር አፈጻጸም በንዑስ አንቀጽ 1.የገቢ ሂሳብ አያያዝ በፊደል ለ/የገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለት የገቢ ሂሳብ በዕለቱ በሂሳብ መዝገብ መመዝገብና በሂሳብ ቋት መወራረ,ስ አለበት ይላል፡፡ በተጨማሪም በአንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 6 በፊደል ለ/የሂሳብ እንቅስቃሴ መነሻ ሰነድ የተዘጋጀላቸው ሂሳቦች በእለቱ በየፋይናንስ ምንጩ በሂሳብ መዝገብ መመዝገብና በሂሳብ ቋት መወራረስ አለባቸው ይላል፡፡ ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲውን የውስጥ ገቢ ሂሳቦች በመመሪያው መሰረት ተሰብስቦ ስለመመዝገባቸው እና ሪፖርት ስለመደረጋቸው ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ግብርና ቢሮ በየዞኑ ያሉትን የግብርና ልማት ሰራተኞችን የትምህርት ደረጃቸውን ከፍ ለማድረግ ከዩኒቨርሲቲው ጋር በገባው ውል መሰረት ለተማሪዎቹ የሚያስፈልገውን ወጪ በ15/3/09 በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 939920 ብር 2,932,660.00 እና በ09/07/09 በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 939921 ብር 2,150,550.00 በድምሩ ብር **5,083,210.00** ለዩኒቨርሲቲው በገቢ ደረሰኝ ገቢ የተደረገው ገንዘብ በትክክል ተመዝግቦ ለታለመለት ዓላማ ስለመዋሉ ኦዲት ሲደረግ፣ ገቢም ሆነ ወጪው በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (TR) ተመዝግቦ ሪፖርት ያልተደረገ በመሆኑ ገቢ የሆነው ገንዝብ በትክክል ለታለመለት ዓላማ ስለመዋሉ ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

2.1.2 ስጋት፣

ማናቸውም ገቢ እና ወጪ በመመሪያው መሰረት በሂሳብ እንቅስቃሲ መዝገብ ላይ ተመዝግቦ ሪፖርት የማይደረግ ከሆነ የመንግስት ውስን ሀብት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡

2.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ማናቸውም የገቢም ሆነ የወጪ ሂሳብ እንቅስቃሴ በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት ተመዝግቦ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡ ስለዚህ በገቢም ሆነ በወጪ ተመዝግቦ ሪፖርት ያልተደረገ ሂሳብ ተጣርቶ ምክንያቱ መቅረብ አለበት፡፡ ለወደፊትም መሰል ስህተት እንዳይፈጠር ዩኒቨርሲቲው ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግበት ይገባል፡፡

2.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

በምዝገባ ሂደቱ ላይ የግንዛቤ ክፍተት ቢኖርም በዚህ ስራ መስክ ላይ የሰው ኃይል እጥረት የነበረብን ሲሆን ለቀጣይ የበጀት ዓመት ያለብንን የሰው ሃይል እጥረት በመፍታትና የግንዛቤ ክፍተት ስልጠናዎችን በመስጠት የምናስታካከል መሆኑን እንገልጻለን፡፡

2.2.1 ግኝት፣ ከተከታታይ ትምህርት ክፍል የተሰበሰበ ገቢ በሚመለከት፣

የፌዴራል መንግስት መስሪያቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ-8 የሂሳብ አያያዝ ዝርዝር አፈጻጸም በንዑስ አንቀጽ 1 .የገቢ ሂሳብ አያያዝ በፊደል ለ/የገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለት የገቢ ሂሳብ በዕለቱ በሂሳብ መዝገብ መመዝገብና በሂሳብ ቋት ላይ መወራረ,ስ አለበት ይላል፡፡ በተጨማሪም በዚሁ መመሪያ በአንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 6 በፊደል ለ/የሂሳብ እንቅስቃሴ መነሻ ሰነድ የተዘጋጀላቸው ሂሳቦች በእለቱ በየፋይናንስ ምንጩ በሂሳብ መዝገብ ላይ መመዝገብና በሂሳብ ቋት ላይ መወራረስ አለባቸው ይላል፡፡

- ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲውን የውስጥ ገቢ ሂሳቦች በመመሪያው መሰረት ተሰብስቦ ስለመመዝገባቸው እና ሪፖርት ስለመደረጋቸው ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ዩኒቨርሲቲው በተከታታይ የትምህርት ፕሮግራም ከሚያስተሚራቸው ተማሪዎች የሰበሰበውን ገቢ በ22/10/09 በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 940457 ብር **302,319.00**፣ በ02/03/09/ በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 940451 ብር **1,010.00** እና በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 940458 ብር **3,750** እና በ25/05/09/ በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 940456 ብር **331,044.00** በድምሩ ብር **638,123.00** በሂሳብ መደብ 1443 ተመዝግቦ የተሰበሰበው ሂሳብ ገቢም ሆነ ወጪው ተመዝግቦ ሪፖርት ያልተደረገ እና ስለወጪውም የሚገልጽ ምንም ማስረጃ የለሌ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

2.2.2 ስጋት፣

ማናቸውም ገቢ እና ወጪ በመመሪያው መሰረት በሂሳብ እንቅስቃሲ መዝገብ ላይ ተመዝግቦ ሪፖርት የማይደረግ ከሆነ የመንግስት ውስን ሀብት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

2.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ማናቸውም የገቢም ሆነ የወጪ ሂሳብ እንቅስቃሴ በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት ተመዝግቦ ሪፖርት መደረግ አለበት፡፡ ስለዚህ በገቢም ሆነ በወጪ ተመዝግቦ ሪፖርት ያልተደረገ ሂሳብ

ተጣርቶ ምክንያቱ መቅረብ አለበት፡፡ ለወደፊትም መሰል ስህተት እንዳይፈጠር ዩኒቨርሲቲው ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግበት ይገባል፡፡

2.2.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

ከ2.1.1. ግኝት ጋር ተመሳሳይ በመሆኑ ለቀጣይ የምናስተካክል መሆኑን እንገልጻለን፣

2.3.1 ግኝት፣ በፋይናንስ ምንጩ ያልተመዘገበ ገቢ፣

የፌዴራል መንግስት መስሪያቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ-7 የሂሳብ ሰነዶችና መዛግብት አያያዝና አጠቃቀም በንዑስ አንቀጽ 5.በየዕለቱ የተሰበሰበ ገንዘብ በገቢ ደረሰኝ ማጠቃለያ መሂ/64 ተጠቃሎ ገቢ መደረግ አለበት ይላል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው በ2009 በጀት ዓመት የሰበሰበውን ገቢ በመመሪያው መሰረት መንግስት ባሳተመው ደረሰኝ ተሰብስቦ ተጠቃሎ ገቢ ስለመደረጉ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- ዩኒቨርሲቲው ከግብርና ውጤቶች ሽያጭ በየዕለቱ የተሰበሰበው ገቢ በመ/ሂ1 የተመዘገበ ቢሆንም፣ በመመሪያው መሰረት በመሂ/64 መመዝገብ ሲገባው፣ ህጋዊነትና ዕውቅና የለሌው ወረቀት በማሳተም በማጠቃለል በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (TR) በሂሳብ መደብ 1455 ብር 652,674.49 የተመዘገበ መሆኑና በውስጥ ገቢ በ1900 መመዝገብ ሲገባው፣ በፋይናንስ ምንጭ በመደበኛ በጀት በ1800 ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

2.3.2 ስጋት፣

ማናቸውም ገቢ ተሰብስቦ ምዝገባ ሲካሄድ ሚኒስቴር መ/ቤቱ እውቅና በሰጣቸው የገቢ ደረሰኝ የማይመዘገብ ከሆነ መመሪያ ከመጠሱ በተጨማሪ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡በውስጥ ገቢ በ1900 መመዝገብ ሲገባው በመደበኛ ሂሳብ በ1800 የሚመዘገብ ከሆነ የተሰበሰበው ገቢ ላይታወቅ ይችል ይሆናል፡፡

2.3.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ማናቸውንም የሂሳብ እንቅስቃሴ ሚኒስቴሩ ባወጣቸው ወይም እውቅና በሰጣቸው የሂሳብ ሰነዶች መመዝገብ አለበት፡፡ በተጨማሪም ማንኛውም የውስጥ ገቢ ሂሳብ መመሪያው በሚፈቅደው መሰረት በ1900 መመዝገብ አለበት፡፡

2.3.4.የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

ቀደም ሲል ሃሮማያ ዩኒቨርሲቲ ስር በነበርንበት ወቅት ሲሰራ በነበረበት እየሰራን ቢሆንም ስህተት መሆኑን ግንዛቤ ካገኘት በኋላ በትክክለኛው በተሰጠን አቅጣጫ የምናስተካክል መሆኑን እና የምዝገባ ስህተቱንም የምናስተካክል መሆኑን እንገልጻለን፡፡

2.4.1 ግኝት፣ ከተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች መቀነስ የነበረበት የሥራ ግብር፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በቀን 07 ጥር 2005 በቁጥር 6.4.0/637/22 በተፃፈ ደብዳቤ ለድህረ ምረቃ ተማሪዎች ለቤት ኪራይ ድጋፍ፣ ለፎቶ ኮፒ፣ ለፅህፈት መሣሪያ ግዥ ድጋፍ፣ የትራንስፖርት አበል ድጋፍ እና ተዛማጅ አገልግሎቶች የሚፈፀሙ ክፍያዎች በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀጽ.3 ከፍደል"ሀ"እስከ"ሸ"ተዘርዝረው ነፃ ከተደረጉት ውስጥ የማይካታቱ በመሆናቸው ግብር የሚከፈልባቸው መሆኑን አሳውቀዋል፡፡ በተጨማሪም የመንግስት መ/ቤቶችና ልማት ድርጅቶች እንዲሁም ሌሎች ድርጅቶችና ተቋማት ከተቀጣሪዎቻቸው ሊቀንሱት የሚገባውን የስራ ግብርን በተመለከተ በቁጥር 1አውግ-54/ በቀን 9 ነሐሴ 2000 በተፃፈ ደብደቤ በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀጽ 3 ከግብር ነፃ ከተደረጉ ገቢዎች በስተቀር ማናቸውም ክፍያ ወይም ጥቅም ከወር ደመወዝ ጋር እየተደመረ ግብር እንደሚከፈልበት ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ አሳውቀዋል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው በሀገር ውስጥ ለሚማሩት መምህራን መመሪያው በሚፈቅደው መሰረት የሚከፈላቸው ጥቅማ ጥቅሞች ከደመወዝ ጋር ተደምሮ የስራ ግብር መቀነስ ሲገባው፣ ከሐምሌ 2008ዓ.ም እስከ ሰኔ 30/2009 ዓ.ም ከተከፈላቸው ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም በአጠቃላይ ብር **48,686** መቀነስ የነበረበት የስራ ግብር ያልተቀነሰ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

2.4.2 ስጋት፣

መቀነስ ያለበት የስራ ግብር ተቀንሶ ወደ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት ገቢ ካልሆነ የመንግስት የበጀት አሸፋፈን ስርዓትን ሊጎዳ ይችላል፡፡

2.4.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

መቀነስ ሲገባው ያልተቀነሰ የስራ ግብር ከሚመለከታቸው ሰራተኞች ተሰብስቦ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ገቢ ሊሆን ይገባል፡፡ ለወደፊትም እንደዚህ ዓይነት ስህተት

እንዳይደገም የገቢ ግብር አዋጅ፣ መመሪያና ደንቦችን መሰረት ያደረገ አሰራር ሊከተል ይኖርበታል፡፡

2.4.4. <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

ከሚማሩ መምህራኖች የሚሰጣቸው ጥቅማ ጥቅምን በተመለከተ በሀረማያ ዩንቨርስቲ ስር በነበርንበት ወቅት ስንሰራ በነበረው መልኩ እየሰራን ስለሆነ መመሪያ የማይፈቅድ መሆኑን ግንዛቤ ስላገኘን ቀጣይ የምናስተካክል መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡

2.5.1 <u>ግኝት</u>፣ <u>ያልተቀነሰ የተጨማሪ እሴት ታክስና ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀናሽ፣</u>

የፌዴራል መንግስት የገቢ ግብር አዋጅ 286/1994 አንቀጽ 53 ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብርን ቀንሶ ስለማስቀረት ንዑስ አንቀጽ 3.ግብር ተቀንሶ ገቢ ማድረግ ያለበት ሰው በወሩ ውስጥ ከተከፈይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ቀሪ መደረግ የሚገባውን አጠቃላይ ሂሳብ ከወሩ መጨረሻ ጀምሮ ባሉት 10 ቀናት ውስጥ ለግብር ሰብሳቢው ባለስልጣን ገቢ ማድረግ አለበት ይላል፡፡ በተጨማሪም በገዥው ተይዘው ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም የወጣው መመሪያ ቁጥር 27/2004 ዓ.ም አንቀጽ-3 ንዑስ አንቀጽ-1/ወኪል መ/ቤቱ ከብር 50,000/ሃምሳ ሽህ/ በላይ ዋጋ ያላቸው የዕቃ ወይም የአገልግሎት ግዥ መፈጸም የሚችለው ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከተመዘገቡ ታክስ ከፋዮች ብቻ ነው ይላል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው የዕቃና የአገልግሎት ግዥ በመመሪያው መሰረት ማከናወን ሲገባው፡-

- የመኪና ጥገና አገልግሎት ከሞኢንኮ ኢ.ማ ግዥ በመፈጸም ብር 139,162.25 ክፍያ ሲፈጽም የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 18,151.60 እና ከተከፋይ ሂሳብ ተቀናሽ ብር 2,420.21 ያልተቀነሰ መሆኑ፣
- የግንባታ ዕቃዎች ከመለሰ ጌታነህ የአጠና ሽያጭ ግዥ በመፈጸም ብር 54,666 ክፍያ ሲፈጽም የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 7,130.35 እና የተከፋይ ተቀናሽ ታክስ ብር 950.71 ያልተቀነሰ መሆኑ፣
- የደንብ ልብስ ግዥ ከሠላም የልብስ ስፌት ድርጅት ግዥ በመፈጸም ብር 63,000.00 ለተከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 8,217.39 እና የተከፋይ ተቀናና ታክስ ብር1,095.65 ያልተቀነሰ መሆኑ፤

- ለተማሪዎች ምግብነት የሚያገለግል ፓስታ ከአህመድ አብዱላሂ ግዥ በመፈጸም ብር 147,800 ክፍያ የፈጸመ ቢሆንም፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 19,278.26 መቀነስ ሲገባው ያልተቀነሰ መሆኑ፣
- ለተማሪዎች ምግብ አገልግሎት የሚውል የበሬ ሥጋ፣ ቀይ ሽንኩርት፣ ድንችና ካሮት ከቡርቃ ጋሌቲ የህ/ሥ/ማህበር ግዥ በመፈጸም ብር 779,573.76 የተከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 101,683.53 እና ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀናሽ ብር 13,252.75 በድምሩ ብር 115,241.33 ያልተቀነሰ መሆኑ፣
- የግንባታና የጥገና ዕቃዎች ከሱራፌልና መድህኒት የመስታወት ንግድ ስራ ማህበር ግዥ በመፈጸም ብር 154,830.00 የተከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር **20,195.20** ያልተቀነሰ መሆኑ፣
- የምጣድ ዕቃዎች ከፋሪስ የኤሌትሪክ ዕቃዎች መሸጫ ድርጅት ግዥ በመፈጸም ብር 69,750.00 ክፍያ የተፈጸመው የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር **9,097.83** ያልተቀነሰ መሆኑ፣
- የተለያዩ የግንባታ ዕቃዎች ከብሩክ ታይትና ወንድዬ የእንጨትና ብረታ ብረት ስራ ድርጅት ግዥ በመፈጸም ብር 196,285.00 ክፍያ የተፈጸመው የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 25,602.39 ያልተቀነሰ መሆኑ፣

በአጠቃላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር **221,439.16** እና ከተከፋይ ሂሳብ ተቀናሽ ብር **17,719.32** በድምሩ ብር **239,158.48** ከተከፈለው ክፍያ ላይ ተቀንሶ ለግብር ሰብሳቢው መ/ቤት ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ገቢ ያልተደረገ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

2.5.2 ስጋት፣

ማናቸውም ከአገልግሎትም ሆነ ከዕቃ ግዥ መቀነስ ያለበት ግብር ተቀንሶ ወደ ሚመለከተው ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት ገቢ ካልሆነ የመንግስት የበጀት አሸፋፈን ስርዓትን ሊጎዳ ይችላል፡፡

2.5.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ዩኒቨርሲቲው የለአግባብ ሳይቆርጥ የቀራውን ታክስ ከድርጅቶች ሰብስቦ ለግብር ሰብሳቢው ባለስልጣን ገቢ ማድረግ አለበት፡፡ለወደፊትም በአዋጁ ከገቢ ግብር ነፃ ከተደረጉት ግብይተቶች በስተቀር ከማናቸውም የአገልግሎትም ሆነ የዕቃ ግዥ የተጨማር እሴት ታክስና ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀናሽ ታክስ ተቀንሶ ለሚመለከተው ግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ገቢ ማደረግ አለበት፡፡

2.5.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

ከተዘረዘሩት ድርጅቶች ውስጥ ሞኤንኮ የተባለው ድርጅት ቫት ተመዝጋቢ በመሆኑ ሰነዶችን በመመርመር የማስተካከያ ሃሳብ የምንሰጥ ሲሆን ሌሎች ድርጅቶች ግን ቫት ተመዝጋቢ ስላልሆኑ ግብሩን ለመቁረጥ አልቻልንም ምክንያቱም በአካባቢያችን ባሉት ድርጅቶች የደረጃ ማነስ ምክንያት ተመራጭ የሆኑትን ለማስተላለፍ ስላልቻልን፣ አስቸኳይ የምንፈልገውን አቅረቦትና አገልግሎት ግዢ ለማግኘት ስላልቻልን መሆኑን እና ለወደፊት በተሰጠን አቅጣጫ መሰረት የምናስተካክል መሆኑን እንገልጻለን፡፡

3. የወጪ ሂሳብ፣

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች ለታቀደለት ዓላማ መዋላቸውን፣ የዕቃና አገልግሎት ግዥ በመንግስት የግዥ መመሪያ መሠረት መፈጸሙንና የተገዙት ዕቃዎች ገቢ መደረጋቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

3.1.1 ግኝት፣ በሂሳብ እንቅስቃሰ መዝገብ ያልተመዘገበ ወጪ፣

የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ-8 ንዑስ አንቀጽ 2. የወጪ ሂሳብ አያያዝ በፊደል መ/ወጪ የተደረገው ገንዘብ በእለቱ በሂሳብ መዝገብ ላይ ለዚህ ተግባር በተዘጋጀው የኮምፕዩተር ስርዓት መመዝገብና በሂሳብ ቋት ላይ መወራረስ አለበት ይላል፡፡ ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲውን የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፤-

- ዩኒቨርሲቲው ለተቋሙ አገልግሎት የሚውል ማባዣ ማሽን፣ የኮምፕዩተር ጠረጴዛዎች የልብስ ማጠብያ ማሽን፣ የስጋ መፍጫ ማሽን እና ፖዲዮም /podium/ ከኦሜዳድ ኃ/የተ/የግ/ኩባንያ ግዥ በመፈጸም በንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞ/19 ቁጥር 173228 እና 173229 በ29/10/09 ገቢ ተደርጎ በ29/10/09 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 476652 ብር 1,782,996.46 ክፍያ የተፈጸመ ቢሆንም በመመሪያው መሰረት በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (TR) ያልተመዘገበ መሆኑ፤
- ዩኒቨርሲቲው ለተማሪዎች የምግብ አገልግሎት የሚውል ሰርገኛ ጤፍ፣ ሩዝ፣ ዛላ በርበሬና ኮረሪማ ከታሪኩ ጌታሁን ጠቅላላ ንግድ ስራ ግዥ በመፈጸም በንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞ/19 ቁጥር 173025 በ01/08/09 ገቢ ተደርጎ በ01/09/09 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር

091460 ብር 606,036.05 ክፍያ የተፈጸመ ቢሆንም በመመሪያው መሰረት በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (TR) ያልተመዘገበ መሆኑ፣

- ዩኒቨርሲቲው ታርጋ ቁጥር ኢት 4-05760 የሆነ መኪና የጥገና አገልግሎት ግዥ ከሪዩስ ኢንጂነሪንግ አክስዮን ማህበር ግዥ በመፈጸም በ28/10/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 577463 ብር 106,436.26 ክፍያ የተፈጸመ ቢሆንም በመመሪያው መሰረት በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (TR) ያልተመዘገበ መሆኑ፣
- ዩኒቨርሲቲው ለተማሪዎች የምግብ አገልግሎት የሚውል የበሬ ግዥ በመፈጸም በ27/10/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 577029 ብር 78,000 ክፍያ የተፈጸመ ቢሆንም በመመሪያው መሰረት በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (TR) ያልተመዘገበ መሆኑ፣
- ዩኒቨርሲቲው ለህንጻ ጥገና አገልግሎት የሚውል ዕቃዎች ከተለያዩ ድርጅቶች ግዥ በመፈጸም በንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞ/19 ቁጥር 754364 በ30/10/09 ገቢ ተደርጎ በ30/10/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 577524 ብር 30,618.64 ክፍያ የተፈጸመ ቢሆንም በመመሪያው መሰረት በሂሳብ እንቅስቃሰ መዝገብ (TR) ያልተመዘገበ መሆኑ፣
- ዩኒቨርሲቲው ለተማሪዎች የምግብ አገልግሎት የሚውል ስኳር እና የምግብ ዘይት ከኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት እና ከሀማሬሳ የምግብ ዘይት አክስዮን ማህበር ግዥ በመፈጸም በንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞ/19 ቁጥር 172897/173021 በ17/05/09 እና 29/07/09 ገቢ ተደርጎ በ30/10/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 577550 ብር 83,166.95 ክፍያ የተፈጸመ ቢሆንም በመመሪያው መሰረት በሂሳብ እንቅስቃሰ መዝገብ (TR) ያልተመዘገበ መሆኑ፣
- ዩኒቨርሲቲው ታርጋ ቁጥር ኢት 4-26715 የሆነ መኪና የጥገና አገልግሎት ግዥ ከኢትዮጵያ ሞተርና ኢንጂነሪንግ ኩባንያ(ሞኤንኮ) ግዥ በመፈጸም በ30/10/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 577525 ብር 25,846.49 ክፍያ የተፈጸመ ቢሆንም በመመሪያው መሰረት በሂሳብ እንቅስቃሰ መዝገብ (TR) ያልተመዘገበ መሆኑ፣
- ዩኒቨርሲቲው ለተማሪዎች የምግብ አገልግሎት የሚውል ዳቦ ከዚያድ ዳቦ ቤት ግዥ በመፈጸም በንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞ/19 ቁጥር 173325 በ20/10/09 ገቢ ተደርጎ በ26/10/09 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 091487 ብር 95,772.24 ክፍያ የተፈጸመ ቢሆንም በመመሪያው መሰረት በሂሳብ እንቅስቃሰ መዝገብ (TR) ያልተመዘገበ መሆኑ፣

በአጠቃላይ ብር 2,808,873.09 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ተመዝግቦ ወጪ የሆነ ገንዘብ በሂሳብ እንቅስቃሰ መዝገብ (TR) ያልተመዘገበ እና በሪፖርት ያልተካተተ መሆኑን በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

3.1.2 ስጋት፣

ማናቸውም ወጪ በወጪ ሰነድ በተመዘገበው የገንዝብ መጠን በሂሳብ እንቅስቃሰ መዝገብ (TR) ላይ ተመዝግቦ ሪፖርት ካልተደረገ የወጣውን ወጪ ከመደበቁ በተጨማሪ የሂሳብ ሪፖርቱን ትክክለኛነት ሊያሳጣ ይችላል ፡፡

3.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ማንኛውም ክፍያ ሲፈጸም በወጪ ሰነድ በተመዘገበው የገንዝብ መጠን በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (TR) ተመዝግቦ ሪፖርት ካልተደረገ ወጪን ከመደበቁ በተጨማሪ የሂሳብ ሪፖርቱን ትክክለኛነት ስለሚያሰጣ ጉዳዩ ተጣርቶ የማስተካከያ እርምት ሊወሰድበት ይገባል፡፡ ለወደፊት መሰል ስህተት እንዳይፈጣር ዩኒቨርሲቲው እያንዳንዱን የሂሳብ እንቅስቃሴዎች ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግበት ይገባል፡፡

3.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

ካለው የሠራተኞች እጥረት ላይ IBX ላይ ይሰራ የነበረው ሰራተኛ በመልቀቁ የተፈጠረ ስህተት ስለሆነ ለቀጣይ በጀት ዓመት የምናስተካክል መሆኑን እንገልጻለን፡፡

3.2.1 ግኝት፣ የወጪ ሂሳብ በተከፋይ ተመላሽ ሂሳብ መመዝገቡ፣

የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ-8 ንዑስ አንቀጽ 2.የወጪ ሂሳብ አያያዝ በፍደል መ/ወጪ የተደረገው ገንዘብ በእለቱ በሂሳብ መዝገብ ላይ ለዚህ ተግባር በተዘጋጀው የኮምፒዩተር ስርዓት መመዝገብና በሂሳብ ቋት ላይ መወራረስ አለበት ይላል፡፡ ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲውን ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፣

- ዩኒቨርሲቲው ለተማሪዎች የምግብ አገልግሎት የሚውል ዳቦ ከዚያድ ዳቦ ቤት ግዥ በመፈጸም በንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞ/19 ቁጥር 173252 በ06/10/09 ገቢ ተደርጎ በ29/10/09 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 091462 ብር 275,780.50 ክፍያ የተፈጸመው በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (TR) በወጪ መመዝገብ ሲገባው ባልተለመደ

የሂሳብ ምዝገባ በተከፋይ ሂሳብ በመንግስት መ/ቤቶች መካከል ሌሎች ተከፋይ ሂሳቦች ተመላሽ በ5028 ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑ፣

- ዩኒቨርሲቲው ለተማሪዎች የምግብ አገልግሎት የሚውል ሥርገኛ ጤፍ እና ሩዝ ከታሪኩ ጌታሁን ጠቅላላ ንግድ ስራ ግዥ በመፈጸም በንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞ/19 ቁጥር 173274 በ09/10/09 ገቢ ተደርጎ በ01/10/09 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 091463 ብር 175,708.65 ክፍያ የተፈጸመው በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (TR) በወጪ መመዝገብ ሲገባው፣ ባልተለመደ የሂሳብ ምዝገባ በተከፋይ ሂሳብ በመንግስት መ/ቤቶች መካከል ሌሎች ተከፋይ ሂሳቦች ተመላሽ በ5028 ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑ፤

በአጠቃላይ ብር **451,489.15** በወጪ መመዝገብ ሲገባው፣ ባልተለመደ የሂሳብ ምዝገባ በተከፋይ ሂሳብ በመንግስት መ/ቤቶች መካከል ሌሎች ተከፋይ ሂሳቦች ተመላሽ በ5028 ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

3.2.2.ስጋት፣

ወጪዎቹ በወጣው የገንዘብ መጠን በተመዘገበበት ሂሳብ መደብ በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ላይ ሳይመዘገብ በተከፋይ ተመላሽ የሚመዘገብ ከሆነ የወጣውን ወጪ ዝቅ ከማድረጉም በተጨማሪ የሂሳብ ሪፖርቱን ትክክለኛነት ሊያዛባ ይችላል ፡፡

3.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ማንኛውም የሂሳብ ምዝገባ በሰነዱ ላይ ተለይተው በተመዘገበው ሂሳብ መደብ በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ላይ መመዝገብ አለበት፡፡ ስለዚህ በወጪ መመዝገብ ሲገባው በተከፋይ ተመላሽ ሂሳብ የተመዘገበው የማስተካከያ እርምት ሊወሰድበት ይገባል፡፡

3.2.4.የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

ይህ ግኝት ከ3.1.1. ጋር ተመሳሳይ በመሆኑ ለቀጣይ በጀት ዓመት የምናስተካክል መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

3.3.1 ግኝት፣ የትርፍ ሰዓት ክፍያ፣

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ ሰኔ 29 ቀን 2001 ዓ.ም በቁጥር መ/30/ጠ13/36/8/3 የተላለፈው የትርፍ ሰዓት አበል አከፋፈል መመሪያ ተለዋጭ መመሪያ እስክተላለፍ ድረስ መመሪያው ተግባራዊ ሳይደረግ እንድቆይ በቀን 5/13/2001

ዓ.ም በቁጥር መ/30/ጠ13//37/820 በተላለፈው ሰርኩላር የትርፍ ሰዓት አበል እንዳይከፈል ተወስኗል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው ያልተሟላ የሰው ኃይል በተፈቀደው የስራ መደብ ላይ በቅጥር አሟልቶ ዝርዝር ዕቅድ አውጥቶ በዕቅዱ መሰረት በመደበኛ የስራ ሰዓት ማሰራት እየቻለ እና የትርፍ ሰዓት ለመክፈል አስገዳጅ የሆኑ የስራ ክፍሎች ለይቶ በሚመለከተው አካል አስፈቅዶ መክፈል ሲገባው፣ ሳያስፈቅድ ከመመሪያ ውጭ ለተለያዩ የስራ ክፍሎች የትርፍ ሰዓት ሥራ እንደሚከተለው ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

- ለተማሪዎች የዲሲፕሊን ኮሚቴ አባላት፣ ለሬጅስትራር የስራ ክፍል፣ ለተማሪዎች አገልግሎት የስራ ክፍል፣ ለሰው ሀብት አመራር፣ ለላይብረሪ ሰራተኞች፣ ለምግብ ቤት ሰራተኞች፣ ፋስሊቲ ማነጅመንት የሥራ ክፍል፣ ለፋርም አስተዳደር ሰራተኞች፣ ለአካዳሚክና ሪሰርች ምክትል ፕሬዚዳንት ሰራተኞች እና ለተለያዩ የሰራ ክፍል ሰራተኞች በአጠቃላይ ብር 476,221.57 የሚመለከተው አካል ሳይፈቅድ ከደንብና መመሪያ ውጭ የተከፈለ ሲሆን የተከፈላቸው ሰራተኞች ስለመስራታቸው የሚገልጽ የሰዓት መቆጣጣሪያ ቅጽ ከወጪ ሰነዱ ጋር ባለመቅረቡ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

3.3.2.ስጋት፣

ማናቸውም ክፍያ በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት ተግባራዊ ካልሆነ የመንግሰት ውስን ሀብት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል

3.3.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ማናቸውም የመንግስት ገንዘብ ክፍየ ደንብና መመሪያን መሰረት ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡

የሰው ኃይል ዕጥረት ያለበት የስራ ክፍል ተለይቶ ባለው ክፍት የስራ መደብ ላይ በቅጥር ተሟልቶ በእቅድ ተይዞ ስራው እንድሰራ ከማድረግ በተጨማሪ የትርፍ ሳዓት ለመክፈል አስገዳጅ የሆኑ የስራ ክፍሎች ተለይቶ የሰው ሀብት እና ፐብሊክ ሰርቪስ ሚኒስቴር አስፈቅዶ መከፈል አለበት፡፡

3.3.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

ተቋሙ አዲስ ከመሆኑ ጋር ካለው የሠራተኛ እጥረት የተነሳ በተፈጠረው የሥራ ጫና ምክንያት የተከፈለ ሲሆን ለቀጣዩ በጀት ዓመት በተፈቀዱልን መዋቅሮች ላይ የሰው ኃይል በማሟላት እና አስፈላጊ ለሆኑን ቦታዎች በሚመለከተው አካል በማስፈቀድ የምናስተካክል መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

3.4.1 ግኝት፣ በዱቤ የሽያጭ ደረሰኝ የተወራረደ ሂሳብ፣

የፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ቁጥር 9 ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ሊደረግ የሚገባ ጥንቃቄዎች ንዑስ ቁጥር 7 ለተገዛ ዕቃ ወይም አገልግሎት ሂሳብ ሲወራረድ በማስረጃነት መቅረብ ያለበት ኦሪጂናል ደረሰኝ መሆን እንዳለበት መመሪያው ያዛል ። ይሁን እንጂ ዩንቨርስቲው፤

- ከሞር-ቴክ ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የላይብራቶሪ ዕቃዎች ግዥ በመፈጸም ብር 1,650,259 ክፍያ የፈጸመ ሲሆን ድርጅቱ ለተከፈለው ገንዘብ የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ መስጠት ሲገባው የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ በማቅረብ ክፍያው የተፈጸመ መሆኑ፤
- ከሆራይዘን አዲስ ጎማ አክሲዮን ማህበር የተሽከርካሪዎች ጎማ ግዥ በመፈጸም ብር 161,620.63 ክፍያ የፈጸመ ሲሆን ድርጅቱ ለተከፈለው ገንዘብ የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ መስጠት ሲገባው የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ በማቅረብ ክፍያው የተፈጸመ መሆኑ፤

በአጠቃላይ ብር **1,811,879.63** የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ቀርቦ ሂሳቡ መወራረድ ሲገባው በዱቤ የሽያጭ ደረሰኝ ሂሳቡ ተወራርዶ የተገኘ መሆኑን ተረጋግጧል ።

3.4.2 ስጋት፣

አቅራቢዎቹ ላቀረቡት ዕቃዎች ወይም ለሰጡት አገልግሎት የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ከልሰጡ ሽያጫቸውን ሊደብቁ ስለሚችሉ መንግስት ከአመታዊ የገቢ ሽያጭ ላይ የሚገኘውን ገቢ ሊያጣ ይችላል።

3.4.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ማንኛውም ክፍያ ሲፈጸም ሂሳቡ መወራረድ ያለበት በእጅ የእጅ ሽያጭ ደረሰኝ መሆን አለበት። ስለዚህ ለተጠቀሰው ሂሳብ ደረሰኝ እንዲቀርብ በማድረግና ለወደፊቱም መሰል ስህተት እንዳይደገም የስራ ክፍሉ ትኩረት ሰጥቶበት ክፍያ ሲፈጸም የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ እንድቀርብ ማድረግ አለበት።

3.4.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

በተገለጸልን መሰረት የወደፊት ስራችንን አስተካክለን የምንሰራ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

3.5.1 ግኝት፣ የተሰረዘ እና የተደለዘ የዋጋ ማቅረቢያ፣

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ምዕራፍ-3 አንቀጽ-30 ንዑስ አንቀጽ 1/የመንግስት መ/ቤቶች ከሚከተሉት በአንዱ ወይም ከአንድ በላይ በሆነ ምክንያቶች ጨረታን የመወዳደሪያ ሀሳብን እና የዋጋ ማቅረብያን የግዥ ስምምነት ከመደረጉ በፊት በማናቸውም ጊዜ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ውድቅ ማድረግ ይችላሉ ይላል። በተጨማሪም ምዕራፍ 9 መሰረታዊ የግዥ ድንጋጌዎች ላይ በአንቀፅ 28.5 የመንግስት መ/ቤቱ ብቃት ያለቸው መሆኑን ለማስረዳት ሀሰተኛ መረጃ የያዙ ሰነዶችን ያቀረቡ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ወይም ብቃታቸው ለማረጋገጥ ያቀረቡት መረጃ መሰረታዊ ስህተት ያለበት ወይም የተረጋገጠባቸው ዕጩ ተወዳዳሪዎች ከጨረታ ውጭ ማድረግ እንደሚቻል ደንግጎታል።

- ይሁን እንጂ የዩንቨርስቲውን የ2009 በጀት ዓመት ግዥዎች በመመሪያው መሠረት መከናወናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ከነኢማ ሁሴን የመኪና ጌጣጌጥ ችርቻሮ ንግድ የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች ግዥ በመፈጸም ብር 57,960.00 የተከፈለው አሸናፊው ድርጅት ያቀረበው የዋጋ ማቅረቢያ ሰነድ የተሰርዞ እና ተደልዞ እንዲያሸንፍ ተደርጎ አሸናፊ ሆኖ ግዥ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችሏል።

3.5.2 ስጋት፣

ማንኛውም ግዥ በአዋጅ፣በመመሪያና ደንብ መሰረት የማይከናወን ከሆነ የህግ ጥሰት ከማስከተሉም በተጨማሪ የመንግስት ሀብት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል።

3.5.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ግዥዎች በሚከናወኑበት ሰዓት አድሎ እንዳይፈጠር በዋጋ ማወዳደሪያ ላይ ስርዝ ድልዝ ማድረግም ሆነ ያደረጉትን አቅራቢዎች ማወዳደር ግዥው ፍትሐዊ ስለማያደርግ ውድድሩ የግዥ አዋጅና መመሪያዎችን መሰረት በማድረግ መከናወን አለበት። ለወደፊቱ ስህተቱ እንዳይደገም ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግበት ይገባል።

3.5.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

በተገለጸልን መሰረት ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የምናስተካክል መሆኑን እንገልጻለን።

3.6.1 ግኝት፣ መመሪያን መሰረት ያላደረገ የክፍያ ተመን፣

የፌዴራል መንግስት የፋይናንስ ኃላፍነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6 በፍደል ሀ/የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች የመ/ቤታቸውን ስልጣንና ኃላፊነት ለመወጣትና የጸደቀውን በጀት መሠረት በማድረግ ወጪዎቹን በመፈጸም በኩል መ/ቤታቸውን የመምራትና የመወከል፤ፕሮግራሞችና መስሪያ ቤታቸውን የሚመለከቱ ሕጎች በማስፈጸም በኩል ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው ይላል፡፡ ይሁን እንጂ ዩንቨርስቲው ደንብና መመሪያን መሰረት ያለደረገ በራሱ የክፍያ ስርዓት አውጥቶ እንደሚከተለው ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

- በዩንቨርስቲው ለመምህራን እና ለአስተዳደር ሰራተኞች ለአንድ ቀን ለተደረገው ስልጠና ጥናታዊ ፅሁፍ እና እቅድ አቅራቢዎች በሚል ለ3 ሰራተኞች ለእያንዳንዳቸው ብር 4,000.00፣ ኮማንድ ፖስት አስተባባሪዎች እና አወያዮች በሚል ለ13 ሰራተኞች ለእያንዳንዳቸው ብር 3,000.00፣ የመድረክ ዝግጅት አስተባባሪዎች በሚል ለ8 ሰራተኞች ለእያንዳንዳቸው ብር 1,500.00፣ የመስተንግዶ ኮሚቴ ለሰሩ በሚል ለ7 ሰራተኞች ለእያንዳንዳቸው ብር 700.00 እና ሰነዶችን ለማባዛት ለሰሩ በሚል ለ8 ሰራተኞች ለእያንዳንዳቸው ብር 600.00 በድምሩ ብር 72,700.00 ደንብና መመሪያን መሰረት ባለደረገ የተከፈለ መሆኑ፡
- ዩኒቨርሲቲው የምርምር ፕሮፖዛል ገምጋሚዎች የሙያ ክፍያ በሚል ለ18 ባለሙያዎች ለእያንዳንዳቸው በሰዓት ብር 110 በመክፈል በድምሩ ብር 83,890 ደንብና መመሪያን መሰረት ባላደረገ የተከፈለ መሆኑ፣
- ለመምህራንና ሰራተኞች ለአንድ ቀን ለተሰጠው ስልጠና የስልጠና አስተባባሪዎች በሚል ለ13 ሰራተኞች ለእያንዳንዳቸው ብር 3,000.00፣ የመድረክ አስተባባሪዎች ኮሚቴ በሚል ለ 8 ሰራተኞች ለእያንዳንዳቸው ብር 1,500.00፣ የመስተንግዶ አስተባባሪዎች ኮሚቴ በሚል ለ8 ሰራተኞች ለእያንዳንዳቸው ብር 700.00፣ የማባዥ ስራ ለሰሩ በሚል ለ8 ሰዎቸች ለእያንዳንዳቸው ብር 600.00 እና ጥናታዊ ጽሑፍ አቅራቢዎች በሚል ለ3 ሰዎች ለእያንዳቸው ብር 4,000.00 በመክፈል በድምሩ ብር **73,400** የተከፈለ መሆኑ፣

በአጠቃላይ ብር **229,990** መመሪያን መሰረት ያላደረገ በራሱ የክፍያ ተመን ያለአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

3.6.2 <u>ስጋት፣</u>

የመንግስትን ገንዘብ ከደንብና መመሪያ ውጪ መጠቀም የመንግስት መመሪያን ከመጣሱም በተጨማሪ የመንግስት ውስን ሀብት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

3.6.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ዩንቨርስቲው ማናቸውም ክፍያ ሲያከናውን ደንብና መመሪያን መሰረት ያደረገ ሊሆን ይገበል፡፡ ስለዘህ ከደንብና መመሪያ ውጭ የተከፈለ አግባብነት እንደለሌው ታውቆ ገንዘቡ ተመላሽ ሊያደርግና ለወደፊት ስህተቱ እንዳይደገም የስራ ክፍሉ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግበት ይገባል፡፡

3.6.4. <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

በተገኘው የኦዲት ግኝት ላይ በቂ ግንዛቤ ያልነበረን በመሆኑ ወደፊት በተገለጸልን እና በተሰጠን አቅጣጫ መሰረት የምናስተካክል መሆኑን እንገልጻለን፡፡

3.7.1 <u>ግኝት</u>፣ <u>ከደንብ ውጭ በቀጥታ ግዥ የተፈጸመ፣</u>

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ምዕራፍ-6 አንቀጽ-51 ንዑስ አንቀጽ /1/የመንግስት መ/ቤቶች ከአንድ አቅራቢ ግዥ መፈጸም የሚችሉት በፊደል /ሀ/ ዕቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራው፣ የምክር ወይም ተፈላጊው ሌላ አገልግሎት የሚገኘው ከአንድ ዕጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ በተጨማሪም የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያን እንደገና ለማሻሻል ታህሳስ 2008 ዓ.ም የወጣ አንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ 25.7 በፊደል /ሀ/ የመንግስት መ/ቤቶች በግዥ እቅድ ውስጥ ያልተካተቱ ዋጋቸው ከብር 5,000.00 ያልበለጡ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን በቀጥታ ግዥ ከማናቸውም ሻጭ ድርድት መፈጸም ይችላሉ፡ ፡ሆኖም የግዥዎች ድምር በአንድ በጀት ዓመት ውስጥ ከብር 75,000.00 መብለጥ እንደለሌበት ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው በአዋጁ መሰረት አገልግሎቱ ከአንድ አቅራቢ ብቻ የሚገኝ በመሆኑ ማወዳደር ያልቻለ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ሳያቀርብ እና የመንግስት ሀብት ቆጣቢ በሆነ መልክ ግዥውን ማከናወን ሲገባው፤

- የመኪና ጥገና አገልግሎት ግዥ ከሞኢንኮ አክስዮን.ማህበር ብር 203,973.73፣ ከተስፋዬ አበበ ብር 35,520 እና ከሪዬስ ኢንጂነሪንግ አክስዮን ማህበር ብር 106,406.26 በአጠቃላይ ብር **345,899.99** ከደንብና መመሪያ ውጭ በቀጥታ ግዥ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

3.7.2 ስጋት፣

ማንኛውም ግዥ በአዋጅ፣በመመሪያና ደንብ መሰረት የማይከናወን ከሆነ የህግ ጥሰት ከማስከተሉም በተጨማሪ የመንግስት ሀብት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

3.7.3.የማሻሻያ ሀሳብ፣

ግዥዎች በቀጥታ ከተወሰነ አቅራቢዎች ብቻ የሚገዛ ከሆነ ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ ሊከናወን ስለማይችል እና ግዥው ፍትሐዊ እንድሆን ሁሉንም አቅራቢዎች በሚያሳትፍ መልኩ የግዥ አዋጅና መመሪያዎችን መሰረት በማድረግ መከናወን አለበት፡፡

3.7.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

ካለው የመኪና እጥረትና የስራ ስፋት ጋር የተመጣጠነ ስላልሆነ ጨረታው ግዜ የሚወስድ በመሆኑ የተፈጸመ ሲሆን ለ2010 የበጀት ዓመት በተሰጠን አቅጣጫ መሰረት ገገርዎችን የምንፈጽም መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

3.8.1 ግኝት፣ ግዥዎችን ቆራርጦ በዋጋ ማቅረቢያ የተፈጸመ ግዥ፣

የፌዴራልመንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 24.1/የአዋጁ አንቀጽ 55 እና 56 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የመንግስት መ/ቤቶች አስቀድሞ ማቀድ እስከተቻለ ድረስ ግዥን በግልፅ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈፀም አለባቸው፡፡ ሆኖም ሊታቀዱ ያልቻሉና ወዲያውኑ ጥቅም ላይ የሚውሉ ወይም በጅምላ ሊገዙ ያልቻሉ እና ዋጋቸው በንዑስ አንቀጽ 24.2 በተመለከተው ገደብ ውስጥ ይሆናል ተብሎ የሚገመቱ ግዥዎችን በዋጋ ማቅሪቢያ ግዥ ዘዴ ለመፈፀም ይችላሉ ይላል፡፡ ይሁን አንጂ ዩኒቨርሲቲው የግዥ ፍላጎትን አሰባስቦ ከመግዛት ይልቅ በርካታ ግዥዎችን ከተለያዩ ድርጅቶች ቆራርጦ በዋጋ ማቅረብያ ግዥ የፈጸመ ሲሆን፣

- የግንባታ ዕቃ ግዥ ብር 2,548,013.41፣ የጥገና አገልግሎት ግዥ፣ የመኪና መለዋዋጫና ጎማ ግዥ ብር 853,579.26፣ የደንብ ልብስ እና የመምህራን ጋዋን ግዥ ብር 471,967.43፣ የተለያዩ የህትመት ስራዎች ግዥ ብር 700,103.88 እና የከብቶች መኖ

ግዥ ብር 302,058.5 በዋጋ ማቅረቢ ግዥ የተፈጸመ ሲሆን፣ በአጠቃላይ ብር **4,875,722.48** አንድ ላይ አሰባስቦ ግዥ መፈጸም ሲገባው፣ በመከፋፈል በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ የተፈጸመ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

3.8.2 ስጋት፣

የግዥ ሰርዓትን በጠበቀ መልኩ ግዥ አለማከነወን መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ ሊዳርግናበ ደንብና መመሪያ ሊጣስ ይችላል፡፡

3.8.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ግዥን ቆራርጦ መግዛት የመንግስት ገንዘብን ለብክነት እና ለከፍተኛ ወጪ ስለሚዳርግ የየክፍሉን የግዥ ፍላጎት በማሰባሰብ ግዥ ቢፈጽም በርካታ ተሳተፊ ድርጅቶች በወድድር ስለሚቀርቡና ከዋጋም አኳያ ዝቅተኛ ዋጋ ሊቀርብ ስለሚችል በደንቡ መሠረት ተፈጻሚ ሊሆን ይገባል፡፡

3.8.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

ግዢዎችን በእቅድ ያለመመራትን በተመለከተ በተለይም በግንባታ ዘርፍ ይህንን ክፍተት በቀጣይ ለማሻሻል ተገቢውን ጥረት እናደርጋለን፡፡ ይሁን እንጂ እንዲታወቅልን የምንፈልገው በእቅድም ለመስራት ዩኒቨርሲቲው አዲስ ከመሆኑ የተነሳ የተሟላ የግዢ ሰራተኛ ባለመኖሩ

የተቀበልናቸውን ተማሪዎች የሚያስፈልገውን አገልግሎት ማሟላት ስላለብን ጊዜ የማይሰጡ እንደ መጸዳጃ ቤት ለውሃና መብራት ዝርጋታ ሌሎችም እንዲሁ ለመምህራንና ለሰራተኞች የቢሮ እጥረት ስላለብን በላሜራዎች ለመከፋፈል የሚያስፈልጉ የግንባታ እቃዎችን በከተማችን ከሚገኙ ድርጅቶች በዋጋ ማቅረቢያ በማወዳደር ከአሸናፊው ድርጅት ለመግዛት ተገደናል፡፡ ለቀጣይ ግን ለማስተካከል ግዢዎችን አሰባስበን በመመሪያው መሰረት ለመስራት ጥረት የምናደርግ መሆኑን በአክብሮትእንገልጻለን፡፡

3.9.1 ግኝት፣ ለተማሪዎች የተከፈለ የሞባይል ካርድ፣

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ልዩልዩ ጥቅማጥቅሞችና የደመወዝ ክፍያን በተመለከተ በቀን 13/8/2003ዓ.ም በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ10/75/390 የተጻፈ ደብዳቤ እንደሚገልጸው ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት

የደመወዝ ስኬል እና ጥቅማ ጥቅም የሚወሰነው በሚኒስትሮች ም/ቤት እንደሆነ ገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ የኦዳ ቡልቱም ዩኒቨርሲቲ የሚመለከተውን አካል አስፈቅዶ ክፍያ መፈጸም ሲገባው፣ ከመመሪያ ውጭ ለተማሪዎች ህብረት ተወካይና ለሠላም ፎረም አባላት በሚል በየወሩ ለሞባይል ካርድ ግዥ በመፈጸም በአጠቃላይ ብር 37,400.00 ያለምንም ደንብና መመሪያ አለአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

3.9.2 <u>ስጋት፣</u>

ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ የሚከናወኑ ማናቸውም ክፍያዎች መንግስትን ለተጨማሪ ከመዳረጉም በተጨማሪ የመንግስት ውስን ሀብት ለብክነት ሊያጋልጥ ይችላል፡፡

3.9.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

የህግመሰረት የሌለው ማንኛውም ክፍያ አግባብነት እንደሌለው ታውቆ ለወደፊት በደንብና መመሪያ መሰረት ክፍያዎቹ እንዲከናወን ትኩረት ሊሰጥበት ይገባል፡፡

3.9.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የተማሪዎች ህብረትና የሰላም ፎረምን ለማጠናከር የሚያስፈልጉ ማናቸውንም ወጪዎችን የሚመለከተው አካል በማስፈቀድ የምናከናውን ይሆናል፡፡

3.10.1 <u>ግኝት</u>፣ <u>ስራ ላይ ለሌሉት ሰራተኞ የተከፈለ ደመወዝ፣</u>

የፌዴራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 ክፍል አራት ምዕራፍ አንድ አንቀጽ 32/ የመንግስት ሠራተኞች መደበኛ የስራ ሰዓት እንደየስራው ሁኔታ የሚወሰን ሆኖ በሳሚንት 39 ሰዓት መስራት እንዳለበት አዋጁ ይደነግጋል፡፡ ዩኒቨርሲቲ ለሰራተኞች የሚከፈላቸው ደመወዝ በአዋጁ መሰረት አንድ ሰራተኛ ስራ ላይ ሆነው በሳምንት 39 ሰዓት በወር 156 ሰዓት ስለመስራቱ የሚያረጋግጥበት የሰዓት መቆጣጠሪያ ፎርማ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በዚሁ መሰረት በየወሩ ለሠራተኞች የሚከፈላቸው ደመወዝ ስራ ላይ ላለው ሠራተኛ ስለመከፈሉ ለማረጋገጥ በናሙና ለኦዲት ከተመረጡት የሰዓት መቆጣጠሪያ ፎርማ (አቴንዳንስ) ኦዲት ሲደረግ፣ በመንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥ አንድ ሰራተኛ ስራ ላይ መሆኑ እና አለመሆኑ የሚታወቀው በመደበኛ የስራ ሰዓቱ ተገኝቶ ስራ ላይ ስለመሆኑ የሚገልጽ የሰዓት መቆጣጠርያ ስፎርም ብቻ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው በተለያየ የስራ ክፍል ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞች በቁጥር 55 የሚሆኑ የሰዓት መቆጣጠሪያ ሳይፈርሙና ስራ ላይ ስለመሆናቸው ምንም ማስረጃ ሳይኖር ስራ

ላይ እንዳሉ ተደርጎ አጠቃላይ ብር 108,729.99 ደመወዝ ተከፍሎ መገኘቱን በኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

3.10.2 <u>ስጋት፣</u>

ከመመሪያ ውጭ የሚከናወን ማንኛውም ክፍያ የመንግስትን ገንዘብ ለብክነት ሊያገልጥ ይችላል፡፡

3.10.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ክፍያ መፈጸም ያለበት በሰዓት መቆጣጠሪያ (አቴንዳንስ) መሰረት ሰራተኞቹ ስራ ላይ መሆናቸው ተጣርቶ መከናወን አለበት ፡፡ስለዚህ በአተንዳንስ ላይ ሳይፈረም ስራ ላይ ስለመሆናቸው ሳይረጋገጥ የተከፈለ ክፍያ አግባብነት ስለለሌው የተከፈለው ደመወዝ ተመላሽ ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡

3.10.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

በተቋሙ ውስጥ ያሉት ሰራተኞች ውስጥ በመሆናቸው ስራ ላይ ያልተገኙትን ሰራተኞች ለመቆጣጠር አዳጋች ባይሆንም የእለት ተእለት የመቆጣጠሪያ አቴንዳንስ ቢኖርም ተከታትሎ በአግባቡ የማጠናከር ስራ ከመስራት ዙሪያ ላይ ያጋጠመ ክፍተት እንጂ ማንም ሰራተኛ ሥራውን ሳይሰራ የተከፈለ ክፍያ የሌለ መሆኑን እየገለጽን ለቀጣዩ በጀት ዓመት የእለት እለት የቁጥጥር መረጃዎችን የምናጠናክር መሆኑን እንገልጻለን፡፡

3.11.1.<u>ግኝት፣ ያለአግባብ የተከፈለ ውሎ አበል፣</u>

የመንግስት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል መመሪያ ሰኔ/2004 ዓ.ም የመንግስት ሰራተኞች የሀገር ውስጥ የቀን የውሎ አበል ክፍያ አፈጻጸም አንቀፅ 8 ንዑስ አንቀፅ 1 ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ ለስራ ጉዳይ ከመደበኛው የስራ ቦታው ውጭ ሌላ ስራ ሲያከናውን በዋለበት የክልል ዞን ወይም ወረዳ ከተማ እንዲከፈል ያዛል፡፡ በዚህ አንቀፅ ስር በፊደል (ለ) ሄዶዕለቱን ከስድስት ሰዓት ተኩል በኃላ የሚመለስ ከሆነ ለምሳ እንደሚታሰብለት መመሪያው ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው፤

- ለሁለት ቀን ባዘጋጀው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ለተሳተፉት በለሙያዎች ከተከፈለው ገንዘብ ውስጥ ለውሎ አበል ለ3 ሰው 4*425፣ ለ2 ሰው 5*149፣ ለ1 ሰው 124*5፣ ለ1 ሰው 7*179፣ ለ1 ሰው 6*179 እና ለ1 ሰው 5*179 በድምሩ ብር 10,432 ለሁለት ቀን መከፈል የነበረበት ብር 4,468 ሲሆን በልዩነት ብር 5,964 ያለአግባብ የተከፈለ መሆኑ፣

- ለሁለት ቀን በተሰጠው ስልጠና በሰዓት መቆጣጠሪያ ፊርማ መሰረት የሁለት ቀን መከፈል የነበረበት ለ77 ሰው*179*2=27,566፣ ለ3 ሰው*147*2=882፣ ለ2 ሰው*123*2=492 እና ለ3 ሰው*480*2=2,880 በድምሩ ብር 31,820.00 መከፈል ሲገባው፣ ተከፍሎ የተገኘ ብር 84,257 በልዩነት ብር **52,437** ያለአግባብ የተከፈለ መሆኑ፤-
- የማህበረሰብ አገልግሎት ስልጠና ለተሰጠው በ27/10/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 577223 ብር 13,371.00 ለአስተበባሪዎች፣ ለአሰልጠኞች እና ለአመቻች የተከፈለው መከፈል የነበረበት የውሎ አበል ብር 2,644.00 በልዩነት ብር 10,369.00 የተከፈለ መሆኑ፤
- ከ11/10/09-15/10/09 በተሰጠዉ የሶፍት ዌር ስልጠና ላይ ለተሳተፉ ለአምስት ቀን መከፈል ሲገበዉ ለእያንዳንዳ እናቸዉ የ10 ቀን በመክፈል በቀን 27/10/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 577234 ብር 244,319.00 የተከፈለ ሲሆን መከፈል የነበረበት ብር 118,225 በልዩነት ብር 126,094.00 የተከፈለ መሆኑ፤
- በ22/09/09 በተደረገዉ የገበሬዎች መስክ ጉቢኝት ላይ ለተሳተፉት የቀን ዉሎ አበል የአንድ ቀን መከፈል ሲገበዉ ፤በቀን 6/10/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 334783 ብር 64,791.00 የተከፈለ ሲሆን መከፈል የነበረበትብር 10,247 በልዩነት ብር 54,544 የተከፈለ መሆኑ፤
- በቀን 12/09/09 በቁጥር CE/06/09 በተፃፈ ደብዳቤ ለ30 የጡሎ ወረዳ ገበሬዎች በተሰጠ ስልጠና ለ17 ሰራተኞች የስልጠና አስተባባሪ በሚል በቀን 30/09/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 334704 ብር 20,653.00 የተከፈለ ሲሆን መከፈል የነበረበት በውሎ ገብ አበል ብር 5,163.20 በልዩነት ብር 15,489.75 የተከፈለ መሆኑ፤**አባሪ2**
- በቀን 25/07/09 በተፃፈ ደብዳቤ ለdept FRM NRM SRWSM በተሰጠ ስልጠና ለ 13 ሰራተኞች የስልጠና አስተባባሪ በሚል በቀን 14/09/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 335380 ብር 17,626.00 የተከፈለ ሲሆን መከፈል የነበረበት በውሎ ገብ አበል ብር 4,406.50 በልዩነት ብር13,219.50 የተከፈለ መሆኑ፤
- ለከፍተኛ እና ለመካከለኛ አመራር የግንዛቤ ማስጨበጫ በተሰጠ ስልጠና ለ 13 ሰራተኞች የስልጠና አስተባባሪ በሚል በቀን 25/09/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 335622 የተከፈለ ብር 26,290.80 ከዚህ ውስጥ ያለአግባብ የተከፈለ ብር 13,985.8ሲሆን

መከፈል የነበረበት በውሎ ገብ አበልብር2,810.82 በልዩነት ብር 11,174.95 የተከፈለ መሆኑ፤

- በቀን 11/09/09 ለተመራቂ ተማሪዎች የስነምግባር ናፀረሙስና ግንዛቤ ማስጨበጫ በተሰጠ ስልጠና ለ10ሰራተኞች የስልጠና አስተባባሪ በሚል በቀን 20/10/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 334948 ብር 10,386.36 የተከፈለ ከዚህ ውስጥ ያለአግባብ ብር5,640.00 የተከፈለ መከፈል የነበረበት በውሎ ገብ አበል ብር 787.80 በልዩነት ብር 4,629 የተከፈለ መሆኑ፤

በአጠቃላይ ብር **293,921.20** በመመሪያው መሰረት ክፍያ መከናወን ሲገባው፣ መከፈል ከነበረበት በላይ በልዩነት ውሎ አበል ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

3.11.2 ስጋት፣

የመንግስትን ገንዘብ ከደንብና መመሪያ ውጭ መጠቀም የመንግስትን መመሪያ ከመጣሱም በላይየመንግስትን ውስን ሀብት ለብክነት ሊያጋልጥ ይችላል፡፡

3.11.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ከመንግስት የክፍያ መመሪያና ደንብ ውጭ የሚከፈል ማናቸውም ክፍያዎች ተቀባይነት እንደለሌው ታውቆ ደንብና መመሪያን መሰረት ያደረገ አሰራር መከተል አለበት፡፡ አለአግባብ የተከፈለውም ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡

3.11.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

ግንዛቤ ማነስ የተሰራ በመሆኑ ወደፊት ማንኛውንም የምንከፍላቸውን ክፍያዎች መመሪያ ደንብን በተከተለ መልኩ የምንፈጽም መሆኑን እንገልጻለን፡፡

4. የተሰብሳቢ ሂሳብ፣

4.1 ግኝት፣

የፌዴራል መንግስት ሂሳብ አያያዝ እና አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 የሂሳብ አያያዝ አፈፃፀም ንዑስ አንቀጽ 4 የተሰብሳቢ ሂሳብ አያያዝ በፊደል (መ) ተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብበት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ተገልጿል፡፡ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲውን የ2009 በጀት ዓመት የፋይናንስ አፈፃፀም ስርዓት ኦዲት ሲደረግ፣ ከተለያዩ ግለሰቦች እና ድርጅቶች የሚሰበሰብ

የመንግስት ገንዘብ በተሰብሳቢ ሂሳብ የሚታዩ ሂሳቦች መወራረድ ባለባቸው ወቅት መወራረድ ሲገባው፣

- የመንግስት ሰራተኞች ቅድሚያ ክፍያ /Advance to staff 4203/ ይህ መለያ ቁጥር በባለበጀት መስሪያ ቤት ሠራተኞች የሚፈለግ ሲሆን፣ ብር 161,539.21 በ2009 በጀት ዓመት ለሰራተኞች የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ በወቅቱ መወራረድ ሲገባው እስከ ሰኔ 30/2009 ያልተወራረደ መሆኑን፣
- የግዥ ቅድሚያ ክፍያ /purchase Advance 4211 /ይህ መለያ ቁጥር ለግዥ ሰሰራተኞች የሚሰጥ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ ሲሆን በመንግስት መመሪያ መሰረት መወራረድ ያለበት ሰባት የስራ ቀናት መብለጥ እንዳለበት መመሪያው ቢያዝም በ2009 በጀት ዓመት ለግዥ ሰራተኞች የተሰጠ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ ብር 566,179.27 እስከ ሰኔ 30/2009 ያልተወራረደ መሆኑን፣
- ሌሎች /others 4274/ ይህ መለያ ቁጥር በሌሎች የመለያ ቁጥር የማይሸፈኑ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን ለመመዝገብ የሚያገለግል ሲሆን ይህ ገንዘብ በአጭር ጊዜ ውስጥ መወራረድ የነበረበት ተሰብሳቢ ሂሳብ ቢሆንም ብር 1,856,428.22 ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እንደሚሰበሰብ ተደርጎ በሌጀር ላይ በተሰብሳቢ ተመዝግቦ ቢታይም ከባንኩ የሚሰበስብ ስለመሆኑ ምንም ማስረጃ የለሌ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ ብር 2,584,146.70 ተሰብሳቢ ሂሳቦች በወቅቱ መወራረድ ሲገባው እስከ ሰኔ 30/2009 ሳይወራረድ መገኘቱን በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል

4.2 ስጋት፣

የመንግስት ገንዘብ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ በደንብና መመሪያ መሰረት በወቅቱ ተሰብሲቦ ገቢ ካልተደረገ የመንግስት የበጀት አሸፋፈን ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከማድረሱም በተጨማሪ ከቆይታ ብዛት ወደ ማይሰበሰቡበት ደረጃ ሊደርሱ ይችላሉ፡፡

ተሰብሳቢ ሂሳቦች ባለቤቱ ተለይቶ በማስረጃ ተደግፎ በግልጽ ካልታወቀ በተሰብሳቢ የተያዘው ገንዘብ ሳይሰበሰብ ሊቀር ይችላል፡፡

4.3 **የማሻሻያ ሀሳብ፣**

ማናቸውም ተሰብሳቢ ሂሳብ በመንግስት መመሪያና ደንብ መሰረት ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፡፡ በተጨማሪም በግለሰቦች እና በድርጅቶች እጅ የሚገኝ ተሰበሳቢ ሂሳቦች በመንግሥት የፋይናንስ መመሪያ መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡ ለእያንዳንዱ ተሰብሳቢ ሂሰብ ከማን እንደሚሰበሰብ ባለቤቱ ተለይቶ ዝርዝር መግለጫ/ኤጂንግ አናላይስስ/ መቅረብ አለበት፡፡ ማስረጃ የለሌላቸው ተሰብሳቢ ሂሳቦች ተጣርቶ ለእያንዳንዱ ተቀጽላ ሌጀር ተከፍቶለት ከማን እንደሚሰበሰብ በግልጽ መቀመጥ አለበት፡፡

4.4 **የሥራ አመራሩ ምላሽ፣**

- ለሰራተኞች ቅድመ ክፍያ ተሰጥቶ ዘግይተው ያወራረዱ ሲሆን በIBX ውስጥ ያልተመዘገበ በመሆኑ፣
- የግዢ ሠራተኞች በ Advance ወስደው ያወራረዱትን ሂሳብ ተቀናሽ ያልተደረገ በመሆኑና የምዝገባ ስህተት መሆኑን፣
- ሌሎች (Others 4274) በተመለከተ የሰራተኞች ደሞዝ በባንክ እንደሚከፈል ይታወቃል፡፡ ሆኖም ለባነክ የተላከው ክፍያ ሰነድ ሲመዘገብ በተጠቀሰው የገንዘብ መጠን በተሰብሳቢነት ባንክ ላይ በምዝገባ ስህተት የተገኘ በመሆኑ ባጠቃላይ በክፍሉ ውስጥ ባለብን የሰው ሃይል እጥረት የተነሳ በቦታው (IBX) ላይ ይሰራ የነበረው ድንገት በመልቀቁ የተፈጠረ ስህተት ስለሆነ ለቀጣይ ስራችን የምናስተካክል መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

5. **የተከፋይ ሂሳብ፣**

5.1 **ግኝት፣**

የፌዴራል መንግስት ሂሳብ አያያዝ እና አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 የሂሳብ አያያዝ አፈፃፀም ንዑስ አንቀጽ5 ሀ.ማናቸውም ወደፊት ክፍያ የሚፈጸምባቸው ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብነታቸውን የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ ሲቀርብና ስልጣን ባለው አካል ሲፈቀድ በተከፋይ ሂሳብነት መያዝ እንዳለበት ተገልጿል፡፡ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲውን የ2009 በጀት ዓመት የፋይናንስ አፈፃፀም ስርዓት የተለያዩ ተከፋይ ሂሳቦች ለባለመብቱ አካል ተከፍሎ በወቅቱ ሂሳቡ መወራረድ ሲገባው፣

- ልዩልዩ ተከፋይ ሂሳቦች /sundry creditors 5002/ ይህ መለያ ቁጥር ከችሮታ ጊዜ ተከፋይ ሂሳቦች በስተቀር ሌሎች ማናቸውም ተከፋይ ሂሳብ ሲሆን ለግለሰቦች የሚከፈል ሂሳብ ብር 78,365 በ2009 በጀት ዓመት በተከፋይ ሂሳብነት የተያዘ ሂሳብ እስከ ሰኔ 30/2009 ያልተወራረደ መሆኑ፤
- የጡረታ መዋጮ ተከፋይ ሂሳብ /pension contribution payable 5003 / ይህ የሂሳብ መደብ ከሰራተኞች እየተሰበሰበ ለጡረታ ፈንድ ገቢ መሆን ያለበት ተከፋይ ሂሳብ ሲሆን በአጭር ጊዜ ውስጥ ተከፍሎ መወራረድ የሚገባ ሂሳብ ብር **227,196.13** በ2009 በጀት አመት በተከፋይነት የተያዘ ቢሆንም ለጡረታ ፈንድ ገቢ መደረግ ሲገባው እስከ ሰኔ 30/2009 ተከፍሎ ያልተወራረደ መሆኑ፤
- የደመወዝ ተከፋይ ሂሳቦች/ salary payable 5004/ይህ መለያ ቁጥር ለሰራተኞች የሚከፈለውን ደመወዝ የገንዘብ ልክ ለመመዝገብ የሚያገለግል ሲሆን፤ክፍያው ለሚገባቸው ሰራተኞች ተከፍሎ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሂሳቡ መወራረድ ሲገባው ብር **58,913.20** እስከ ሰኔ 30/2009 ተከፍሎ ያልተወራረደ መሆኑ፤
- በመንግስት መ/ቤቶች መካከል ሌሎች ተከፋይ ሂሳቦች /other payable within government 5028/ ይህ መለያ ቁጥር በሁለት የባለበጀት መ/ቤቶች ወይም በባለበጀት መ/ቤት እና በክልል መካከል ያሉ ሌሎች ተከፋይ ሂሳቦች ለመመዝገብ የሚያገለግል ሲሆን ፤ክፍያው ለሚገባቸው ተከፍሎ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሂሳቡ መወራረድ ሲገባው እስከ ሰኔ 30/2009 ብር**1,896,132..80** ተከፍሎ ያልተወራረደ ሲሆን፤ዩኒቨርሲቲው በሂሳብ መደብ 5028 መዝግቦ ብር 1,896,132.80 ለማን እንዳሚከፈል ምንም ማስረጃ ሳይኖር በተከፋይ ሂሳብ የተያዘ መሆኑ በኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- ሌሎች ማስያዣ ሂሳብ /others deposit 5054/ በሌሎች መለያ ቁጥር ያልተሸፈኑ በመንግስት የተያዘ ሂሳቦች የሚመዘገብበት ሲሆን ብር 9,770.64 ለግለሰብ የሚከፈል ሂሳብ ሲሆን በወቅቱ ተከፍሎ መወራረድ ያለበት ሂሳብ እስከ ሰኔ 30/2009 ዓ.ም ያልተወራረደ መሆኑ፤

በአጠቃላይ ብር **2,270,377.77** ተከፋይ ሂሳቦች ለባለመብቱ ተከፍሎ መወራረድ ሲገባው ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡

5.2 ስጋት፣

የተከፋይ ሂሳብ ለባለመብቱ ድርጅት፤መ/ቤት ወይም ግለሰብ በወቅቱ አለመተላለፉ ገንዘቡ ለታቀደለት ዓላማ እንዳይውልና በበጀት አጠቃቀም ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

ተከፋይ ሂሳቦች ለማን እንደሚከፈል ባለቤቱ ተለይቶ በግልጽ ካልተቀመጠ ለመክፈል ሊያስቸግር ይችላል፡፡

5.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ዩኒቨርሲቲው ማናቸውም ተከፋይ ሂሳብ በመንግስት መመሪያ እና ደንብ መሰረት ለድርጅቶችና ለግለሰቦች መከፈል ያለበት ተከፋይ ሂሳብ ተከፍሎ ሂሳቡ በወቅቱ መወራረድ አለበት ፡፡

ዩኒቨርሲቲው ከሠራተኞች የሰበሰበውን የጡረታ ገንዘብ ለጡረታ ፈንድ ገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤት ገቢ በማድረግ ሪፖርት ሊቀርብ ይገበል፡፡የደመወዝ ተከፋይ ሂሳቦች ለሰራተኞች ተከፈሎ ሂሳቡ መወራረድ አለበት፡፡

ለእያንዳንዱ ተከፋይ ሂሰብ ለማን እንደሚከፈል ባለቤቱ ተለይቶ ዝርዝር መግለጫ/ኤጂንግ አናላይስስ/ መቅረብ አለበት፡፡ ማስረጃ የለሌላቸው ተከፋይ ሂሳቦች ተጣርቶ ለእያንዳንዱ ተቀጽላ ሌጀር ተከፍቶለት ለማን እንደሚከፈል በግልጽ መቀመጥ አለበት፡፡

5.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

- ክፍያ ለሚመለከተው አካል ክፍያው ተከፍሎ (IBX) ላይ ያልተመዘገበ (ያልተቀናነሰ) በመሆኑ የምዝገባ ስህተት መሆኑ
- የጡረታ ተከፋይ መዋጮ በተመለከተ የሰራተኞች ደሞዝ በትሬዠሪ ሲጠየቅ እዛው ተቀንሶ የሚመጣ በመሆኑ እዛው የሚቀር ስለሆነ የምዝገባ ስህተት መሆኑ፡፡
- የደሞዝ ተከፋይን አስመልክቶ ለሰራተኛው የደሞዝ ክፍያ ተፈጽሞና በ5004 ተመዝግቦ በ(IBX) ያልተመዘገበና ያልተወራረደ የምዝገባ ስህተት መሆኑን፣
- በመንግስት መስሪያ ቤቶች መካከል ሌሎች ተከፋይ ሂሳቦችን አስመልክቶ፣ ሰነዶችን በመመርመር የማስተካከያ እርምት የምንወስድ መሆኑን በአጠቃላይ የምዝገባ ስህተቶችን በተመለከተ የሰራተኛ እጥረት ክፍተታችንን በማማላት ለቀጣይ የምናስተካክል መሆኑን እና ሰነዶችን በመመርመር የሚስተካከል መሆኑ ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

6. በጀት፣

6.1 ግኝት፣

በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/2 መሠረት የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ የመንግስት መ/ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈፀም እንደማይቻል ይገልጻል፡፡በተጨማሪም የፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ 648/2001 ክፍል 6 የመንግስት ገንዘብ ክፍያ አንቀጽ 30 በዚህ አዋጅ አንቀጽ 23 እስከ 26 በተደነገገው መሠረት ካልሆነ በስተቀር በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ በበጀት አዋጁ ለተመለከተው የመንግስት መሥሪያ ቤት እንዲከፈል በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን በላይ ክፍያ መፈጸም እንደማይቻል ተገልጿል፡፡ይሁን እንጂ ለዩኒቨርሲቲው ለ2009 በጀት ዓመት ከተፈቀደው እና ማስተካከያ ከተደረገለት በኋላ የ12 ወር የፋይናንስ አፈፃፀም ኦዲት ሲደረግ፣ በልዩ ልዩ የወጪ ሂሳብ መደቦች ውስጥ ከመደበኛ በጀት ብር **27,815,706.14** ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑን ተረጋግጧል

6.2 ስጋት፣

ዩኒቨርሲቲው በ2009 በጀት ዓመት የተፈቀደለት በጀት በአግባቡ አለመጠቀሙ ሊደርስበት ካቀደው ግብ እንዳይደርስ ከማድረጉም በተጨማሪ የሀገሪቱን ውስን ሃብት ያለጥቅም እንዲቀመጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡

6.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ያልተሰራበትን በጀት በተመለከተ ዩኒቨርሲቲው በተጨባጭ ሊሰራ ካቀደው ተግባር ጋር በማገናዘብ እና አፈፃፀሙን በመገምገም የበጀት ዝግጅቱ የሚሻሻልበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለበት፡፡ ከወዲሁም የበጀት አፈጻጸሙን በማየት በደንቡ መሠረት ዝውውር በማድረግ ሥራ ላይ ሊያውል ስለሚገባ ለወደፊቱ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

6.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

በጀትን አስመልክቶ የተገኘ ግኝት ላይ በተሰጠን አቅጣጫ መሰረት የወደፊት ስራችንን የምናስተካክል መሆኑን እንገልጻለን፡፡

7. ንብረት፣

7.1.1 ግኝት፣ የተሽከርካሪ የውስጥ ቁጥጥር ደካመ መሆኑ፣

የፌዴራል መንግስት የተሽከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 በክፍል 1 አንቀፅ 10 የመንግስት ተሽከርካሪዎች መለዋወጫ ዕቃ አጠቃቀም እና ቁጥጥር በንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) መሰረት ማንኛውም የመ/ቤቱ ወይም በራሱ እንዲያሽከረክር የተፈቀደለት ሀላፊ ያረጀ ጎማና ቼርኪን ጨምሮ የመለዋወጫ ዕቃ በአዲስ እንዲተካለት ሲጠይቅና የጥያቄው ትክክለኛነት አግባብ ባለው ባለሙያ ሲረጋገጥ የተቀየረው መለዋወጫ ዕቃ ወደ ዕቃ ግምጃ ቤት ተመላሽ ተደርጎ በተሽከርካሪው የግል ማህደር ውስጥ ተመዝግቦ እንዲቀመጥ መደረግ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡በተጨማሪም በክፍል 2 አንቀፅ 6 በንዑስ አንቀፅ (1) ስር የመንግስት መ/ቤት በግዥ፤በስጦታ፤በዝውውር እንዲሁም በሌሎች መንገድ ተረክቦ ለሚጠቀምበት ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ የተለየ የግል ማህደር በመክፈት በማህደሩ ውስጥ መረጃዎች መዝግቦ መያዝ እንዳለበት ይገልፃል፡፡ይሁን እንጂ የዩንቨርስቲውን የ2009 በጀት ዓመት የተሽከርካሪ አያያዝና ቁጥጥር በመመሪያው መሠረት መከናወናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤-

- እያንዳንዱ ተሽከርካሪዎች የግል ማህደር ተከፍቶላቸው የተሽከርካሪው አይነትና ሞዴል፤የቻሲና የሞተር ቁጥሮች፤የሚጠቀመው የነዳጅ አይነት፤የተገዛበት ወይም በመ/ቤቱ የዋለበት ዓ.ም፤የተሽከርካሪው ዋጋ እና የባለቤትነት መታወቅያ ደብተር ፤ በኪሎ ሜትር የሚጠቀመው የነዳጅ ፍጆታ፤የዘይትና የቅባት ፍጆታው፤የጥገናው ወጪ፤በነማን ይዞታ ስር እንደነበረ የሚገልፅ የህይወት ታሪክ መዝገብ መረጃ መኖር ሲገባው የለሌ መሆኑ፡-
- በዩኒቨርሲቲ ስር ያሉ የተለያዩ ተሽከርካሪዎች ብዛት፤ዓይነት፤የሚገኙበት ሁኔታ በጀት አመቱ እንደተጠናቀቀ ለመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ሪፖርት መቅረብ ሲገባው ያልቀረበ መሆኑ፡-
- የሚሰራና የማይሰራ መኪና ተለይተው ከነምክንያቱ በማስረጃ የተደገፈ መረጃ መኖር ሲገባው መረጃ የለሌ መሆኑ፤-
- ዩኒቨርሲቲው የአሽከርካሪዎች የውስጥ የቁጥጥር ስርዓትና ደንብ መኖር ሲገባው ባለመኖሩ ምክንያት በአንዳንድ አሽከርካሪዎች ቸልተኝነትና ከጥንቃቄ ጉድለት የተነሰ

ተሽከርካሪዎቹ በየጊዜው ለግጭት እንደሚዳረጉ እና ዩኒቨርሲቲው ላልተገባ ወጪ እየተዳረገ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ችለናል፡፡

- ተሽከርካሪዎቹ ጥገና ሲደረጉ በባለሙያ አስፈላጊው ክትትል እንደማይደረግና በጥገና ወቅት የተቀየሩት ተለዋጭ ዕቃዎች በገቢነት የማይመዘገቡ መሆኑ፡-
- የዩኒቨርሲቲው ንብረት የሆነ ሳንሎንግ(የሕዝብ አዉቶቢስ) ተሽከርካሪ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር /ሊብሬ/ የሌለ መሆኑ፤-
- የሠለዳ ቁጥር ኦሮ 4-01801 የሆነች ኮስቴር መኪና መወገድ ከለበት በንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት ሰይወገድ ወይም ተጠግኖ አገልግሎት መስጠት የሚችል ከሆነ በባለሙያ ተረጋግጦ ተጠግኖ አገልግሎት መስጠት ሲገባው ሳይጠገን ለረጅም ጊዜ ያለአገልግሎት ቆሞ ፀሐይና ዝናብ እየተፈራረቀበት የሚገኝ መሆኑ፤
- በቁጥር አምስት የሚሆኑ ትራክተሮች በመ/ቤቱ የግል ማህደር የሌላቸውና መስራት አለመስራታቸው ተጣርቶ መወገድ ከለባቸው መወገድ ሲገባቸው ወይም ተጠግኖ አገልግሎት የሚሰጡ ስለመሆናቸው ሳይጣራ በየቦታው ተበታትነው የሚገኙ መሆኑን በኦዲቱ ለማወቅ ችለናል፡፡
- የነዳጅ ግዥ ስርዓትን እንደተመለከትነው ግዥው መፈጸም ያለበት በኩፖን ሆኖ በግዥ ሰራተኞች መገዛት ቢገባውም ተሽከርካሪዎቹ በዩኒቨርሲቲ አከባቢም ሆነ ለስራ ታዞ ወደ መስክ በሚወጡበት ወቅት ግዥው የሚፈጸመው በሹፌሮች መሆኑን በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በዩኒቨርሰቲው ስር የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ለሹፌሮች በማክፋፈል በስማቸው ተመዝግቦ የሚገኝ ቢሆንም አንድ ተሽከርካሪ ለደህንነቱ ሲባል በአንድ ሾፌር እጅ መያዝ ቢገባው አንድ መኪና በተለያዩ ሾፌር እጅ የሚገኝ በመሆኑ ተሽከሪካሪው ለብልሽት ከመጋለጡም በተጨማሪ እድሜ እንደማይኖራቸው አመላካች እንደሆነ በኦዲቱ ወቅትለማወቅ ተችሏል፡፡

7.1.2 <u>ስጋት፤</u>

ማንኛውም የመንግስት ተሽከርካሪዎች የግል መረጃዎች ከሌለው የመንግስት ደንብና መመሪያ ከመጣሱም በላይ አስፈላጊው ጥንቃቄ እና እንክብካቤ ላይደረግለት ይችላል፡፡

7.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፤

ለእያንዳንዱ ተሸከርካሪ የግል ማህደር ተከፍቶላቸው የመኪናዎቹን ሙሉ ማስረጃ ተመዝግቦ መያዝ አለበት፡፡ያለአገልግሎት የቆሙት ትራክቴሮች እና መኪና ይስራ አይስራ በባለሙያ ተረጋግጦ መወገድ ከለበት ማስወገድ እና ተጠግኖ አገልግሎት ልሰጡ የሚችሉ ከሆነ አገልግሎት እንድሰጡ መደረግ አለበት፡፡ለመንግስት ተሸከርካሪዎች ልዩ ትኩረት በመስጠት የውስጥ የቁጥጥር ስርዓት ተዘርግቶ ከላይ የተጠቀሱት ክፍተቶች የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድበት ይገባል፡፡

7.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

በተሰጠን አቅጣጫ መሰረት ያሉንን ተሽከርካሪዎች አጠቃላይ መረጃዎችን በማጠናከር አስፈላጊ የሆኑ የክትትልና ቁጥጥር ስራዎችን በቀጣይነት የምንሰራ ይሆናል፡፡

7.2.1 ግኝት፤ የቋሚና የአላቂ ንብረት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች፤

የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 አንቀጽ 5 የመመሪያው አላማ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በእጃቸው ያለውን የመንግስት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ፤የመጠቀም፣ የመቆጣጠር እና አገልገሎት ላይ በማይውልበት ጊዜ በወቅቱና በተገቢው መንገድ ማስወገድ እንዳለበት ያዛል። በተጨማሪም በፌደራል መንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 8/2003 በስራ ክፍሎችና ሠራተኞች መካከል ሊኖር የሚገባውን መዋቅራዊ ግንኙነቶች በመመስረት ሊነጣጠሉ የሚገባቸውን ስራዎችና ኃላፊነቶች በተለያዩ ሰዎች ተከፋፍለው እና ተለይተው እንዲሰሩ የሚያስችል ስልት ዘርግቶ ተግባራዊ መድረግ እንዳለበት ተገልጿል። ይሁን እንጂ ዩኒቨርስቲው፡-

- በቋሚ ንብረት ክፍል ቢን ካርድም ሆነ ስቶክ ካርድ የማይጠቀም በመሆኑ የንረብት ወጪ እና ቀሪ ስለማይታወቅ ማመዛዘኛ ይማይሰራ መሆኑ፤
- የ2009 በጀት አመት የንብረት ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም ገቢ እና ወጪ መመዛዘኛ ያልተሰራ መሆኑ
- ቋሚ እቃዎች በመዝገብ ወይም በኮምፒዩተር ተመዝግቦ ወጪው እና ገቢው መመዛዘኛ መሰራት ሲገባው የማይመዛዘን መሆኑ፤
- ለእያንዳንዱ ቋሚ ንብረት መለያ ቁጥር መሰጠት ሲገባው ሙሉ በሙሉ ያልተሰጠ መሆኑ፡

- በቋሚ ንብረት ክፍል ዉስጥ አገልግሎት ይስጥ አይስጥ በባለሙያ ተረጋግጦ መወገድ ካለበት በንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት ማስወገድ ወይም ተጠግኖ አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ አገልግሎት መስጠት ሲገባው፤ በርካታ ዴስክቶ ኮምፒዩተር ከነሙሉ አክሰሰሪ፤የፎቶኮፒማሽን፤የተለያዩ ብዛት ያላቸው የላይብራቶሪዕቃዎች፤የአልጋብረት፤በጣም ብዛት ያላቸው የላይብረሪ መደርደርያዎች ፤የብረትበሮች፤የብረት ጠረጴዛዎች፤የብረት ወንበሮች፤ጎማ፤የተለያዩ ቶነር፤የተማሪዎች መመገቢያ ጠረጴዛዎች ፤ ፍሪጆች፤የእንጨት ሎከሮችና ጠረጴዛዎች፤ሽልፎች ፤ በሮችና መስኮቶች ፤ በአጠቃላይ በጣም በርካታ ቋሚ ዕቃዎች በተመለሽ ንብረት ክፍል ዉስጥ እና በቋሚ ንብረት ክፍል ዉስጥ እንድሁም በጸሐይ ላይ ተዘርግፎ የሚገኙ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡
- አሮጌ እና አዲስ ተገዝቶ የሚገቡ ቋሚ ዕቃዎች ተለይቶ መቀመጥ ሲገባው በቋሚ ንብረት ክፍል ዉስጥ ተቀላቅሎ የሚገኝ መሆኑ፤
- ከትምህርት ሚኒስቴር የመጣ የተማሪዎች የብረት ሼልፍ ጊዛዊ መጥለያ ተሰርቶለት መቀመጥ ሲገባው ግቢ ዉስጥ በየቦታው ተከማችቶ የሚገኝ መሆኑ፤
- በቆርቆሮ የተሰረ ንብረት ክፍል ዉስጥ የተለያዩ የመመገቢያ ጠረጴዛዎች ፤የንብ ቀፎዎች ፤ጀኔሬተሮች፤የእህል መዝሪያ ማሽኖች እና የእህል መዉቂያ ማሽኖች አገልግሎት ይስጡ አይስጡ በባለሙያ ተረጋግጦ አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ አገልግሎት እንድሰጥ ማድረግና የሚወገድ ከሆነም መወገድ ሲገባው ያለአገልግሎት በንብረት ክፍል ዉስጥ የሚገኝ መሆኑን በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

<u>አላቂ ንብረትን በተመለከተ</u>

- የተማሪዎች የምግብ ጥሬ እቃ ከአላቂ ንብረት ጋር አንድ ላይ ተቀላቅሎ የሚገኝ መሆኑ፤
- በአላቂ ንብረት ስቶር ውስጥ የተለያዩ ቋሚ ንብረት ቦይለር፤ የላሜራ ብረት እና ቆርቆሮ ተቀላቅሎ የሚገኝ መሆኑ፤
- በአላቂ ንብረት ክፍል ዉስጥ የሰራተኞች ደንብ ልብስ ከመጠን በላይ በመገዛቱ ምክንያት የተረፈ በስቶሩ ዉስጥ ተከማችቶ የሚገኝ መሆኑ፤
- በአላቂ ንብረት ስቶር ውስጥ የሚገኝ የመኪና ባትሪ በቁጥር 12 የሚሆን ሲሚንቶ የተበላሸ በቁጥር 12 ከራጢት የሚሆን የምርት ማሳደጊያ ማዳበሪያ በኩንታል 13 የሚሆን

ከአላቂ ንብረት ክፍል ተለይተው በየራሳቸው ንብረት ክፍል መቀመጥ ሲገባው ካለቦታው ለቆጠራ በማይመች ቦታ የሚገኝ መሆኑን በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

- በአላቂ ንብረት ክፍል ውስጥ የሚገኙ ንብረቶች ቢን ካርድና ስቶክ ካርድ ጅምር ሥራ ቢኖም ሙሉ በሙሉ ተመዝግቦ በወቅቱ ማመዛዘኛ የማይሰራ መሆኑ፤
- በቁጥር 30 ኩንታል የሚሆን በሎቄ በ2007 ዓ.ም በዩኒቨርሲቲ የተመረተ በወቅቱ መሸጥ ሲገበዉ ሳይሸጥ በነቀዝ እየተበላ መሆኑ፤
- የከብቶች መኖ በቁጥር 20 ኩንታል የሚሆን መወገድ ሲገበዉ በእንስሳት መኖ ክፍል ውስጥ የሚገኝ መሆኑ፡

በአጠቃላይ የቋሚ ዕቃም ሆነ የአላቂ ዕቃዎች የቆጥጥር ስርዓቱ በጣም ደካመ መሆኑን በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

<u>የተማሪዎች ምግቤት በተመለከተ</u>

- የተማሪዎች የምግብ ጥሬ እቃ በአላቂ ንብረት ክፍል ዉስጥ ተከማችቶ የሚገኝ መሆኑ፡
- ጊዜው ያለፈበት የተማሪዎች የምግብ ግብዓት መካሮኒ1.788ኪ.ግ፤አተር ክክ 1.647 ኪ.ግ ፤ ምስር ክክ 1.761 ኪ.ግ እና ምስር ድፍን1.120 ኪ.ግ መወገድ ሲገባው ያልተወገደ መሆኑን በኦዲቱ ለማረጋጋጥ ችለናል፡፡

7.2.2 ስጋት፣

የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ደካማ በመሆኑ መንግሥት በውስን ሀብት ግዥ የፈፀመው ንብረት ለብክነት የሚያጋልጥ ከመሆኑም በላይ በስራው ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

7.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

የንብረት ክፍሉን አደረጃጀት በማስተካከል የንብረት መቆጣጠሪያ መዝገቦችንና የቁጥጥር የአሠራር ሥርዓትን ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ዩንቨርስቲው የመንግስት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ፣ የመጠቀም፣ የመቆጣጠር እና አገልገሎት ላይ በማይውልበት ጊዜ በወቅቱና በተገቢው መንገድ ማስወገድይኖርበታል፡፡

7.2.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

በተሰጠን አቅጣጫ መሰረት ያለውን ችግር ለመቅረፍ በቂ የእቃ ማከማቻ መጋዘን በመገንባት በቦታው ላይ የተመደቡትን አዳዲስ ሰራተኞች በማሰልጠን የቁጥጥርና ክትትል ስርአታችንን ከፍ በማድረግና መጠገን ያለባቸው ተጠግነው ስራ ላይ ሊውሉ የሚችሉ

ንብረቶችን በማስጠገንና አገልግሎታቸውን የጨረሱ እቃዎችን በህጉ መሰረት ባደረገ መልኩ በማስወገድ አስፈላጊውን መፍትሄ የምንሰጥ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

8. ልዩ ልዩ፣

8.1.1 ግኝት፤ ያለአግባብ የተፈጸመ ቅጥር፤

የፌዴራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 ክፍል ሦሥት ምዕራፍ አንድ አንቀጽ 13 ክፍት የሥራ መደቦችን በሠራተኛ ስለማስያዝ ፤ ንዑስ አንቀጽ 1/ በብሔረሰብ ፤በፆታ፤በሐይማኖት፤በፖለትካ አመለካከት፤በአካል ጉዳት፤በኤች አይቪ/ኤድስ ወይም በሌላም ሁኔታ በስራ ፈላጊዎችም ሆነ በመንግስት ሠራተኞች መካከል ልዩነት መማድረግ የተከለከለ ነው ይላል፡፡ በተጨማሪም በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2/በክፍት የስራ መደብ ላይ ሠራተኛ የሚመደበው ለሥራ መደቡ የሚጠየቀውን ተፈላጊ ችሎታ የሚያሟላና ከሌሎች ተወዳዳሪዎች ጋር ተወዳድሮ ብልጫ ያለው ሆኖ ሲገኝ ብቻ እንደሆነ አዋጁ ይገልጻል፡፡ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲውን የ2009 በጀት ዓመት ኦዲት ሲናከናውን የሠራተኞችን ቅጥር ስለትክክለኛነቱ ለማረጋገጥ በወሰድነው የኦዲት ናሙና መሰረት ከአዋጁ ውጭ እንደሚከተለው ቅጥር ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

- ዩኒቨርሲቲው በኮምፒዩተር ሳይንስ ዲፓርትመንት ለመምህርነት አቶ ጀማል አብራሂም ኢሳ መንግስት ያወጣውን አዋጅ በሚቃረን ያለምንም ውድድር ቅጥር የፈጸመ መሆኑ፤
- የጊዜያዊ ቅጥር ኮሚቴ ቃለ-ጉባኤ እንደሚያሳየው ግለሰቡን የፈተኑት በቀን 15/06/2017 (8/10/09) ሲሆን ደመወዝና ጥቅማጥቅም እንድከፈለው የቅጥር ደብዳቤ በቀን 29/09/09 በቁጥር ከ/ሠ/ሀ/ል/ዳ/1374 የተጻፈ ሲሆን ከመቀጠሩ በፊት የቅጥር ደብደቤ መስጠት አግባብ ያልሆነና ተጠያቅነትን ሊያስከትል ስለሚችል ተቀባይነት የለሌው ቅጥር መሆኑ፤
- የካቲት 6/2009 በኢትዮጵያ ሔራልድ ጋዜጣ በወጠው የመምህራን ቅጥር ማስታወቂያ በኮምፕዩተር ሳይንስ ዲፓርትመንት ላይ ለምዝገባ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ አንድም ሰው ባለመለከተበት እና በልተመዘገበበት ሁኔታ የጊዜያዊ ቅጥር ኮሚቴም ሆነ የሰው ሀብት ስራ አመራርና ልማት ዳይሬክተር በዚያን ጊዜ ለመቀጠር ካመለከቱት አመልከካቾች መካከል መስፈርቱን አሟልቶ ለውድድርና ለቅጥር የበቃ አስመስሎ የጻፉት ደብዳቤ አግባብ እንደልሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡

- ከላይ የተጠቀሱ ጉዳዮች እንደተጠበቀ ሆኖ ለተጠቃሹ ሰራተኛ በቀን 12/3/2010 በቁጥር ከ/ሠ/ሀ/ል/ዳ/7085 በተጻፈው ደብዳቤ ከጥቅምት 07/ቀን2010 ዓ.ምጀምሮ በሌክቸረር ደረጃ ወራዊ ደመወዝ 10,470 እና የቤት አበል800 እየተከፈላቸው እንድሰሩ ሁለተኛ የቅጥር ደብዳቤ የተሰጣቸው መሆኑን በኦዲቱ ለማረጋገጥ ችለናል፡፡

በአጠቃላይ የተደረገው የቅጥር ሁኔታ ፍትሐዊነት የለሌው፤ግልጸኝነት የጎደለ፤አዋጅን የሚቃረን፤ተጠያቅነትን የሚያስከትልና አግባብነት የለሌው ስራ መሆኑን በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

8.1.2 ስጋት፤

የመንግስትን አዋጅ፤ደንብና መመሪያን መሰረት ያላደረገ በተቋምና በግለሰቦች ፍላጎት የሚሰራ ማንኛውም የመንግስትን ሀብት ለብክነት ከማጋለጡም በተጨማሪ ተጠያቅነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

8.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፤

ከመንግስት ከአዋጅ፤ደንብና መመሪያ ውጭ የሚከናወኑ ማንኛውም ቅጥር አግባብነት እንደለሌው ታውቆ እስከ አሁን የተከፈለው ደመወዝና ጥቅማጥቅም ተመላሽ ሆኖ ያለአግባብ የተፈጸመ ቅጥር ተቋርጦ እንደገና ማስታወቅያ ወጥቶ በውድድር ቅጥሩ መከናወን አለበት፡፡

8.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

በኦዲት ሪፖርቱ እንደተገለጸው ቀደም ሲል በኮምፒውተር ሳይንስ ዲፓርትመንት የተወዳደሩት ግለሰብ የቅጥር ሂደቱ ላይ በተመለከተ በአመዘጋገብ ችግር ምክንያት የተፈጠረውን ስህተት መሰረት በማድረግ ቅጥሩ ሙሉ በሙሉ የተሰረዘ ሲሆን በድጋሚ የቅጥር ህጉን መሰረት አድርጎ በወጣው ማስታወቂያ መሰረት ግለሰቡ ብቸኛ ተወዳዳሪ በመሆኑ ህግና ስርአቱን ተከትሉ ቅጥሩ የተከናወነ መሆኑን እና የቅጥር ሂደቱን የሚያሳይ መረጃ በወቅቱ ከፌደራል ኦዲተር ቢሮ ለመጡ አባላት ያቀረብን መሆኑን እና ቅጥሩ በአግባቡ መሰረት የተከናወነ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

በመጨረሻም ለተደረገልን መልካም የስራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡